
ኢፕድ
# አዲስ ዘመን
ዓርብ
81ኛ ዓመት ቁጥር 273 ሰኔ 3 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር
DERBA CEMENT

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ



# “ኢትዮጵያና ሶማሊያ ሁለንተናዊ ግንኙነታቸውን በማጠናከር ብልጽግናን ያረጋግጣሉ”

## - ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያና ሶማሊያ የጋራ ባህላቸውን፣ ደህንነታቸውንና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታቸውን በማጠናከር ብልጽግናን እንደ ሚያረጋግጡ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአዲሱ የሶማሊያ ፕሬዚዳንት ሀሰን ሼህ ማህሙድ በዓለ ሲመት ላይ በሞቃዲሾ ተገኝተው ባደረጉት ንግግር፣ በሶማሊያ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር በመደረጉ መደሰታቸውን ገልጸዋል።

ያለጎረቤቶቻችን ትብብርና ድጋፍ በተናጠል ሰላምና ልማትን ማረጋገጥ አንችልም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፣ ኢትዮጵያና ሶማሊያ የጋራ ባህላቸውን፣ ደህንነታቸውንና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታቸውን በማጠናከር ብልጽግናን እንደሚያረጋግጡም ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ ባለፉት ዓመታት የጋራ እድገት እና ልማት ትብብር ላይ የተመሰረተ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ በመከተሏ ሁለቱ አገሮች በቀጣናዊ ትስስር አዲስ መንገድ መክፈታቸውን ተናግረዋል።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት የተገኙ ዲፕሎማሲያዊ ድሎች ከአዲሱ የሶማሊያ ፕሬዚዳንት ጋር በጋራ በመስራት ይበልጥ እንደሚጠናከሩ እና እንደሚሰፉም ነው ያስታወቁት።

በኢትዮጵያ እና በሶማሊያ መካከል ያለው

“ኢትዮጵያና ሶማሊያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# «የህወሓት አመራሮች ለመኖሪያ ቤታቸው መብራት እያገኙ የአይደር ሆስፒታል ሥራ ማቆሙ የስግብግብነታቸው ማሳያ ነው»

## አቶ መስፍን ደሳለኝ

ማእረግ ገ/እግዚአብሔር

አዲስ አበባ፡- የህወሓት አመራሮች ለግል መኖሪያ ቤታቸው መብራት እያገኙ የአይደር ሪፈራል ሆስፒታል በነዳጅእጥረትምክንያት ሥራማቆሙ የስግብግብነታቸው ማሳያ ነው ሲሉ የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ትዴፓ) ምክትል ሊቀመንበር አቶ መስፍን ደሳለኝ ገልፀዋል።

«የህወሓት አመራሮች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አክንውሚ አዲስና

# ኢትዮጵያ ስንዴ ወደ ውጭ ለመላክ በሚያስችል ቁመና ላይ መሆኗን የአፍሪካ ልማት ባንክ ገለፀ

ገመቹ ከድር

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ እስከ ሁለት ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ስንዴ ለጎረቤት ሀገራት የማቅረብ አቅም ያላት ሀገር ነች አፍሪካ ልማት ባንክ ፕሬዚዳንት ገለጹ።

አፍሪካ ልማት ባንክ ፕሬዚዳንት አክንውሚ አዲስና በቅርቡ ጋና አክራ ተካሂዶ በነበረው ዓመታዊ ስብሰባ መዝጊያ ላይ ባደረጉት ንግግር ኢትዮጵያ የስንዴ ምርትን ወደ ውጭ ሀገር ለመላክ በሚያስችል ቁመና ላይ መሆኗን ተናግረዋል ።

ኢትዮጵያ በ650ሺህ ሄክታር መሬት ላይ ሁለት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ሰንዴ ማምረት በሚያስችል ደረጃ ላይ መገኘቷን ከጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ መስማታቸውን ገልጸዋል። በዚህ ዓመት ኢትዮጵያ ከውጭ የምታስገባው ስንዴ እንደሌለና ከሚቀጥለው ዓመት ጀምሮ የሀገሪቱን የማረስ አቅምን በማሳደግ እስከ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር ምርት ወደ ጎረቤት ሀገራት የመላክ እቅድ እንዳላት ከጠቅላይ ሚኒስትሩን መስማታቸውን ተናግረዋል።

እ.አ.አ በ2018 የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች የቆላ ሰንዴን ማምረት ጀመሩ ።በሂደት ወደ 167ሺህ ሄክታር አሳደጉት። ከሁለት ዓመት በኋላም የሰንዴ ምርቱን ወደ 400ሺህ ሄክታር ማሳደግ መቻላቸውን ከጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ መስማታቸውን ፕሬዚዳንቱ ገልጸዋል።

# 44 ሚሊዮን ዜጎች በጤና መድህን አገልግሎት ተጠቃሚ እየሆኑ ነው

ዳግማዊት ግርማ

አዲስ አበባ፡- በአገር አቀፍ ደረጃ በ880 ወረዳዎች እየተተገበረ በሚገኘው ጤና መድህን አገልግሎት 44 ሚሊዮን ዜጎች ተጠቃሚ እየሆኑ እንደሆነ የኢትዮጵያ

44 ሚሊዮን ዜጎች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ኦሮሚያን ይጎብኙ
የብዝሃ-ውበት ምድር!
Website:
https://www.visitoromia.org
Facebook:
https://www.facebook.com/visitoromia/
Instagram:
https://instagram.com/VisitOromia
Twitter:
https://twitter.com/VisitOromia
LinkedIn:
https://linkedin.com/company/visitoromia
YouTube:
https://YouTube.com/visitoromia
Pinterest:
https://Pinterest.com/visit_oromia
Telegram:
https://t.me/visit_oromia
ኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን
www.visitoromia.org

አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ
ADAMA STEEL FACTORY
ሚስማር ከ3 ቁጥር -15 ቁጥር
የበረንዳ
ታይልስ
ኤጋ
መደበኛ
ክላሞ
0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565

UNIC ETHIOPIA
ሕብረት ኢንሹራንስ አማ
THE UNITED INSURANCE COMPANY SC
Tomorrows Company Today'
+251 111 26 34 34
united.insurance@unic-ethiopia.com
ለ ሁሉም የመድን ፍላጎትዎ
ለህይወት
ህጋዊ ግዴታዎ

# የፓስፖርት አገልግሎት ክፍያዎችን በቴሌ ብር በኩል መክፈል የሚያስችል ስምምነት ተደረገ

**ሞገስ ጸጋዬ**



አዲስ አበባ፡- አዲስ ፓስፖርት ለማውጣት፣ ለማሳደስ፣ ለጠፋ ምትክ ለማውጣትና የተበላሸን ለማስተካከል የሚያስችሉ የአገልግሎት ክፍያዎችን ባሉበት ሁነው በቴሌ ብር በኩል መክፈል የሚያስችል የስምምነት ፊርማ ከኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ጋር መፈራረሙን ኢትዮ ቴሌኮም አስታወቀ።

በትናንትናው ዕለት በኢትዮ ቴሌኮም እና በኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት መካከል የፓስፖርት አገልግሎት ክፍያዎችን በቴሌብር በኩል መፈጸም የሚያስችል የስምምነት ፊርማ ተፈራርመዋል።

የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈጻሚ ፍሬሕይወት ታምሩ በፊርማ ሥነ ሥርዓቱ ላይ እንደገለጹት፤ አዲስ ፓስፖርት የሚያወጡ፤ የሚያሳድሱና ምትክ የሚፈልጉ ደንበኞች ቀላል ፈጣን፣ ምቹ እና አስተማማኝ የሆነውን የዘመኑን የዲጂታል ክፍያ ሥርዓት ቴሌ ብርን ተጠቅመው በየትኛውም ጊዜና ቦታ ሆነው የአገልግሎት ክፍያቸውን መፈጸም ይችላሉ።

እንደ ሥራ አስፈጻሚዋ ገለጻ፤ የአጋርነት ስምምነቱ የኢትዮ ቴሌኮም የቴሌብር አገልግሎትን ከፓስፖርት አገልግሎት ክፍያ አሰራር ጋር በማስተሳሰር በየጊዜው እያደገ የመጣውን የደንበኞች የክፍያ አማራጭ ቀላልና አስተማማኝ ያደርጋል።ቴሌብር አዲስ ፓስፖርት ለማውጣት ለማሳደስ፣ ለጠፋ ምትክ ለማውጣት እና የተበላሸ እንዲስተካከልላቸው የሚፈልጉ ደንበኞች የአገልግሎት ክፍያቸውን ባሉበት ቦታ በቀላሉ መክፈል እንደሚያስችላቸው ጠቁመዋል።

ደንበኞች አዲስ ፓስፖርት ለማውጣትም ሆነ ለማሳደስ ወደ ኤጀንሲው ሲሄዱ የሚደርሰውን የገንዘብና የጊዜ ብክነት፤ የጉልበት ድካምና የደላሎች ወከባ በመቀነስ ለደንበኞች ምቹና ቀልጣፋ የአገልግሎት ክፍያ አማራጭ ለማቅረብ ያለመ መሆኑን አስረድተዋል።

የቴሌብር የዲጂታል የክፍያ ሥርዓት ተግባራዊ ከተደረገ ጀምሮ ለዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎት መስፋፋት ጉልህ ሚና ተጫውቷል ያሉት ሥራ አስፈጻሚዋ፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ 20 ሚሊዮን ደንበኞች፤ 82 በላይ ዋና ወኪሎች፣ 69 ነጥብ 8 ሺህ ወኪሎች እና 188 ሺህ ነጋዴዎች ማፍራት መቻሉን አስረድተዋል።

በተጨማሪም በቴሌብር 20 ነጥብ 63 ቢሊዮን ብር የኤሌክትሮኒክ ገንዘብ ዝውውር የተደረገ መሆኑን አመልክተው፤ ከ12 ባንኮች ጋር ከባንክ ወደ ቴሌብር እና ከ10 ባንኮች ጋር ደግሞ ከቴሌብር ወደ ባንክ ገንዘብ ለማስተላለፍ ትስስር መፍጠሩ የዲጂታል የክፍያ ሥርዓት ያለውን ከፍተኛ ተመራጭነት ያሳያል ብለዋል።

በተጣይ ጊዜያትም ኩባንያው ከሌሎች መሰል ተቋማት ጋር በመተባበር የክፍያ ስርዓታቸውን በቴሌብር የሚተገብሩበትን አሰራር በማመቻቸት ደንበኞቻቸው የዲጂታል ክፍያ ሥርዓት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ እየሰራ ነው።የቴሌብር ደንበኞች በአንድ ሥርዓት ሁሉንም ክፍያ ባሉበት ሆነው መፈጸም እንዲችሉ ለማድረግ የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ የሚቀጥልና የዲጂታል ኢትዮጵያን ራዕይ ዕውን የማድረጉ ተግባር ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቁመዋል።

የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር አቶ ብሩህተስፋ ሙሉጌታ፤ ስምምነቱ ዜጎች የተቀላጠፈ አገልግሎት እንዲያገኙና ኤጀንሲው የበለጠ ወደ ዜጎች መቅረብ እንዲችል እገዛ ያደርጋል።ቴክኖሎጂው ያመጣልንን እድል ተጠቅመን ዜጎቻችን የሚፈልጉትን አገልግሎት በጊዜና በጥራት እንዲያገኙ ያግዛል ብለዋል።

በአገልግሎት አሰጣጣችን ሂደት ውስጥ ትልቅ ችግር የነበረው የአገልግሎት ክፍያ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ዜጎች በፓስፖርት ማውጣት ዙሪያ ክፍያቸውን በቴል ብር መክፈል መቻላቸው የሚስተዳጎለውን ችግሩን ይቀርፈዋል፤ እንዲሁም አገልግሎታችንን በጥራትና በፍጥነት እንድናከናውን ያግዛል ሲሉ ገልጸዋል።



# የነዋሪዎችን የቤት ችግር ለመቅረፍ የተለያዩ አማራጮች እየተፈለጉ መሆኑ ተጠቆመ

አዲስ አበባ፡- የነዋሪዎችን የቤት ችግር ለመቅረፍ የተለያዩ አማራጮችን እያፈላለገ እንደሆነ የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ገለጸ።

የከተማ እና መሠረተ-ልማት ሚኒስትር ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን የ2014 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርበዋል።

በዚህ ወቅትም የቤት ችግርን ለመቅረፍ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተለያዩ አማራጮችን እያፈላለገ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

በተለይም ለግሉ ሴክተር ሁኔታዎችን በማመቻቸት፣ የግሉ ሴክተር እየገነባ፣ የራሱን ድርሻ እየወሰደ፣ ዜጎችን የቤት ባለቤት እንዲያደርግ ስትራቴጂ መቀየሱን ሚኒስትሯ ገልጸዋል።

ቤቶች ሲገነቡ የሚያስፈልጉትን መሠረተ-ልማቶች ጭምር ለመገንባት መንግሥት የአስቻይ ሚናውን ለመወጣት እየጣረ ይገኛልም ነው ያሉት ሚኒስትሯ።

ከጦርነቱ በኋላ የተጎዱ ከተሞችን መልሶ ለመገንባት በተደረገው ጥረት የጋሸና እና የኮምቦልቻ መንገዶች ጥገና ላይ መሆናቸውንም ገልጸዋል።

ሆኖም ግን ወደ ቀድሞ ይዞታቸው ለመመለስ በሚደረገው ጥረት ቀሪ ሥራዎች እንዳሉ ሚኒስትሯ መናገራቸውን ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

# ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂን በመጠቀም ዘላቂ ሀገራዊ ዕድገትን ለማምጣት በትኩረት እንደሚሰራ ተገለጸ

**ውብሸት ሰንደቁ**



ዶክተር በለጠ ሞላ

አዲስ አበባ፡- ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂን በመጠቀም ዘላቂ ሀገራዊ ዕድገትን ለማምጣት ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሠራ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶክተር በለጠ ሞላ፤ በሀገሪቱ የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ ዙሪያ ለሚዲያ አካላት ገለፃ አድርገዋል።

ዶክተር በለጠ በሰጡት ገለፃ፤ የኢፌዴሪ የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ ሚያዚያ 2014 ዓ.ም ጸድቋል። የፀደቀው የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲም የመጨረሻ ግቡ በምርምር የታገዙ የቴክኖሎጂና የኢኖቬሽን ውጤቶችን በመጠቀም ሀገራዊ ዕድገትን ማምጣት ነው።

ሳይንስን፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽንን በመጠቀም የተለያዩ ሀገራት ኢኮኖሚያቸውን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ማድረግ ችለዋል ያሉት ሚኒስትሩ በኢትዮጵያም ተመሳሳይ አካሄድ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ዘርፍ የጀመረው በ1968 ዓ.ም ቢሆንም ከዘርፉ ፈጣን ለውጥና ዕድገት ፍላጎት አንፃር እምብዛም በመሆኑ በ2004 ዓ.ም ፖሊሲ የመከለስ ሥራ ተሠርቶ የተለያዩ ውጤቶችን ማስመዝገብ ተችሏል ብለዋል።

የፖሊሲ ክለሳው አስፈላጊነት ላይ ገለጻ የሰጡት ዶክተር በለጠ፤ የ2004 ዓ.ም የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ ምንም እንኳን ውጤት የነበረው ቢሆንም እያጋጠሙን ያሉ ተግዳሮቶች በዘላቂነት ለመፍታት የፖሊሲና ራዕይን አሳቤዎች ለፖሊሲው ክለሳ መነሻ ሆነው ተገኝተዋል ብለዋል።

ተከልሶ ሥራ ላይ የዋለው ፖሊሲም የ2030 ዘላቂ የልማት ግቦችን፤ የአፍሪካ 2063 አጀንዳ እና 2025 የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ስትራቴጅን ታሳቢ በማድረግ የ2014 ዓ.ም ሀገራዊ የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ ተከልሶ ፀድቋል በማለት አብራርተዋል።

በፖሊሲው ክለሳ በዋናነት ትኩረት የተደረጉባቸው ነገሮች የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ዋና ዋና ግቦች፤ የሥራ ዕድል ፈጠራ፤ የሀገሪቱን የውጭ ገቢ መጨመር አጠቃላይ ሀገራዊ ምርትን ማሳደግ እንደሆኑ በመጠቆም አዳዲስ ሀብት መፍጠር እና አካታች ልማትን ለማረጋገጥ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚንና ኢኖቬሽንን የሚያበረታታ ማኅበረሰብ መገንባት ያስችላል ብለዋል።

መንግሥት ለዘርፉ በተሰጠው ከፍተኛ ትኩረት እና በመደበው መዋዕለ ነዋይ በየጊዜው የሚገነቡና የሚደራጁ የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማቶች እንዲሁም አገልግሎቱን ከማስፋት ረገድ በሀገሪቱ እየተመዘገቡ ያሉት አበረታች ውጤቶች ማሳያ መሆናቸውን ዶክተር በለጠ ጠቅሰዋል። ይህም በሰው ኃብት ልማት፤ በምርምርና ልማት ቴክኖሎጂ ልማትና ሽግግር እንዲሁም በፈጠራ ሥራዎች በአጠቃላይም ለኢኖቬሽን ሥርዓቱ በቂ ዕውቀት፣ ክህሎት እና አወንታዊ አመለካከት እየተፈጠረ መምጣቱ ነው ብለዋል።

ሳይንስ ቴክኖሎጂንና ኢኖቬሽንን የመጠቀም ባህሉ የጎለበተ ዜጋ ለማፍራት ለዘርፉ አመራር የሰው ኃይል ማልማት ለሀገራችን ስትራቴጅካዊ ጥቅም ያላቸው መፃኢውን ጊዜ መሰረት ያደረገ እና ተነፃፃሪ ጥቅም በምናገኝባቸው ዘርፎች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እንዲሠራ በፖሊሲው ታሳቢ መደረጉን ሚኒስትሩ አብራርተዋል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ የመወዳደር አቅም ያለው የሰው ኃይል እንዲገነባ ልዩ ተሰጥኦ ላላቸው ዜጎች እንዲሁም በሳይንስና ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን የሙያ ዘርፎች በቂና ብቁ ባለሙያዎችን ገበያና ቴክኖሎጂ ፍላጎትን መሰረት ባደረገ መልኩ ማፍራት ስለሚጠበቅ በፖሊሲው ትኩረት መሰጠቱንም ገልፀዋል።

የአንድ ሀገር ዕድገት ደረጃ በዋናነት የሚለካው ባለው የቴክኖሎጂ አቅምና በዘርፉ መሰረተ ልማት አቅምና ክምችት እንዲሁም ምርታማነት ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ ይህን ለማምጣት እና ዘርፉን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ ካሉት የመንግሥት ከፍተኛ ተቋማት ውስጥ በቴክኖሎጂ ኢኖቬሽን ዙሪያ የተሻለ ልምድ ካላቸው ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር ተቀናጅቶ ለመሥራት በፖሊሲው ትኩረት መሰጠቱን አብራርተዋል።

በሌላ መልኩ በፌዴራል፣ በክልልና በከተሞች ደረጃ የምርምር ተቋማትን በማስፋፋት ዘርፉ ለሀገራዊ ዋና ዋና ችግሮች መልስ እንዲሰጥ በሚያስችል መልኩ እንደሚሠራ ገልፀዋል። ይህም የምርምር እና ስርፀት ሥራዎች በመሠረታዊነትም ዋና ዋና የልማት ችግሮቻችንን ለመፍታት እንዲሁም አቅም መገንባትን ታሳቢ ያደረገ ነው ብለዋል።

ዜና

# በአዲስ አበባ 169 አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ካፒታላቸውን በማሳደግ ወደ መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ተሸጋገሩ

**መዓዛ ማሞ**



አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር 169 አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ካፒታላቸውን በማሳደግ ወደ መካከለኛ ኢንተርፕራይዝነት ተሸጋግረዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥራ ኢንተር ፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ " የኢንተርፕራይዝ ሽግግር ፤ ለኢንዱስትሪ መሠረት!" በሚል መልዕክት የ11ኛ ዙር ኢንተርፕራይዞች የምርቃት መርሐ ግብር ተካሂዷል።

ኢንተርፕራይዞቹ ከአንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር በላይ ካፒታል ያስመዘገቡና ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች የሥራ ዕድል የፈጠሩ ናቸው።ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ ኢንተርፕራይዝነት የተሸጋገሩት 84 በማኑፋክቸሪንግ፣ 77 በኮንስትራክሽን፣ 4 በንግድ ዘርፍ፣ ሦስት በአገልግሎት ዘርፍ እና ሁለት በግብርና ዘርፍ የተሰማሩ እንደሆኑ በመርሐግብሩ ላይ ተገልጿል።

በምርቃት ሥነ ሥርዓቱ ላይ የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ እና የሥራ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ጃንጥራር አባይ እና ሌሎች የከተማ አስተዳደሩ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል። ኢንተርፕራይዞቹ ከ11ዱ ክፍለ ከተሞች የተውጣጡ ሲሆኑ ኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ 23 ኢንተርፕራይዞችን በማስመረጥ የአንደኝነትን ቦታ በመያዝ የዋንጫ ተሸላሚ ሁኗል። አቃቂ ቃሊቲ እና አዲስ ከተማ ክፍለ ከተሞች ደግሞ የሁለተኛና ሶስተኛ ደረጃዎችን በመያዝ የተዘጋጀላቸውን ዋንጫ ተቀብለዋል። የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ባደረጉት የመዝጊያ ንግግር የአገራችንን ሁለንተናዊ ብልጽግና ለማጎናጸፍ ሁሉን አቀፍ ጠንካራ የለውጥ ጎዞ ከተጀመረ ዓመታት መቆጠራቸውን ጠቁመው ፤ ህዝቡ ዋጋ የከፈለበትን ለውጥ ተጠቃሚ መሆን እንዲችል ሌት ተቀን በመስራት ለውጦች እንደተመዘገቡ ተናግረዋል።

እንደ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ገለጻ፤ የለውጡ ጉዞ እና የአገራችን የብልጽግና አጀንዳ ያልተዋጠላቸው የተደራጁ ኃይሎች ለማደናቀፍና ሀገራችንን ለማፍረስ ቢጥሩም አልተሳካላቸውም። እነዚህ አካላት የደቀኑብንን አደጋ በብቃት እና በጽናት በመቋቋም ማንም ምድራዊ ኃይል ሊያስቆመው በማይችል መልኩ የለውጥ ጉዟችንን ቀጥለናል። የኢንዱስትሪ መሰረት የሆኑትን ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ማደራጀት፣ ሁሉን አቀፍ ድጋፍ በመስጠት እና ወደ አምራች ኢንዱስትሪ እንዲሸጋገሩ ለማስቻል የመስሪያ ቦታ ፣ የፋይናንስ ድጋፍ ፣ የገበያ ትስስር ፣የሙያ እና ስልጠና መስጠት ትኩረት ተሰጥቶበት ሲሰራበት መቆየቱን ከንቲባዋ ተናግረዋል።ኢንተርፕራይዞች ችግሮችን በመቋቋም እና በመፍታት ጥረታቸውን አጠናክረው በመቀጠል እና ተኪ ምርቶችን በማምረት አገራዊ አቅም እንዲያጠናክሩ እንዲሁም የሥራ አመራሮች፣ ሰራተኞች እና የግሉ ተቋማት ለኢንተርፕራይዞቹ በተለያየ መንገድ ድጋፍ እንዲሰጡ የአደራ መልዕክታቸውንም አስተላልፈዋል።



አቶ ደበበ ዘውዴ

## ‹‹በከተማም ሆነ በገጠር የጎርፍ አደጋዎችን ለመከላከል የሚያስችሉ ሥራዎች እየተከናወኑ ነው ››

### - የኢትዮጵያ አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ በገጠራማ አካባቢዎችም ሆነ በከተሞች ከክረምቱ ጋር ተያይዞ ሊከሰቱ የሚችሉ የጎርፍ አደጋዎችን ለመከላከል የሚስችሉ ሥራዎች በመከናወን ላይ መሆናቸውን የኢትዮጵያ አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን አስታወቀ።

በኮሚሽኑ የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር አቶ ደበበ ዘውዴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በመጪው የክረምት ወቅት ሊከሰት የሚችለውን የጎርፍ አደጋ ለመከላከል በፌዴራል ደረጃ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችን እንዲሁም በክልል ሴክተር መስሪያ ቤቶችን ያካተተ የጎርፍ ግብረ ኃይል ተቋቁሞ ወደ ሥራ ገብቷል። በአሁኑ ወቅትም በፌዴራልና በክልሎች የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥራዎችን በመሰራት ላይ ናቸው ።

እንደ አቶ ደበበ ገለጻ፤ ግብረ ሀይሉ የጤና፣ የትምህርት፣ የውሃና ኢነርጂ፣ የግብርና ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች እንዲሁም ከአጋሮች እንደ ቀይ መስቀልና የዓለም ምግብ ፕሮግራም ተቋማት የተካተቱበት ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት የመጠባበቂያ እቅድ፣ ተጠቂ ቦታዎች የመለየትና የጎርፍ ካርታ ሥራዎች በመሰራት ላይ ናቸው ። በክረምቱ ምክንያት ምን ሊያስከትል ይችላል የሚሉ ጉዳዮችንም እንዲሁ በቅድመ ማስጠንቀቂያ ደረጃ በመሥራት ላይ ነው።

በቅድመ ማስጠንቀቂያ ተግባራት ጉድኋድ የማጽዳት፣ ተጋላጭ ሰዎችን የማንሳትና መሰል ተግባራት እንደሚከናወኑም አቶ ደበበ አስታውቀዋል።

በኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን አስተባባሪነት ለአጋር አካላት በወረዳ ደረጃ የመከላከል አቅምን ለማጎልበት ሥልጠናዎች እንደሚሰጡ የጠቀሱት አቶ ደበበ፤ ቀይ መስቀል በአፋር፤ በኦሮሚያና በጋምቤላ ክልሎች ሥልጠናውን ለመስጠት ዝግጅቱን ማጠናቀቁን ለአብነት አንስተዋል። በተራራና በወንዝ አካባቢ ያሉትን ጨምሮ በከተማ ያሉ የአደጋው ስጋት ያንዣበበባቸው አካባቢዎችን ከአደጋው ለመከላከል አቅም መፍጠር እንደሚያስፈልግም ተናግረዋል።

አቶ ደበበ፤ በኢትዮጵያ በጦርነት ምክንያት በርካታ ዜጎች ድጋፍ ፈላጊ መሆናቸውንና በርካቶች ደግሞ በተለያዩ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ጉዳት ደርሶባቸው ድጋፍ እየተደረገላቸው እንዳለ ጠቅሰዋል። ይህ እያለ ሊከሰት ይችላል የተባለውን የጎርፍ አደጋ ለመከላከል በአሁኑ ወቅት በትብብርና በቅንጅት መስራት እንደሚያስፈልግም ተናግረዋል። ለዚህም ከግለሰብ ጀምሮ የከተማ አስተዳደሮች የጋራ ሀብትን በማሰባሰብ አቅም መፍጠር ይኖርባቸዋል ነው ያሉት።

“ሴክተር መስሪያ ቤቶች፣ ክልሎች፣ አጋር አካላት፣ ህብረተሰቡ፣ በተቀናጀ ሁኔታ ማን ምን መስራት አለበት የሚለው በፖሊሲ ተቀምጧል። ሁሉም በባለቤትነት ሊመራው ይገባል” ብለዋል።

ጎርፉ ሲከሰት የወባ ወረርሽኝና ሌሎች ተጓዳኝ ችግሮችንም ይዞ ሊመጣ እንደሚችል ገልጸዋል። ይህንን ታሳቢ ያደረገ ዝግጅት እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው፤ ኮሚሽኑ በቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥራው ለሁሉም ክልሎችና ሴክተር መስሪያ ቤቶች መረጃውን ተደራሽ ማድረግ እንደቻለ አክለው ገልጸዋል።



# “ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ትኩረት ይስጠን” አሉ የራያ እና አላማጣ ተፈናቃዮች

አዲስ አበባ፡- ዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ትኩረት ሊሰጠን ይገባል ሲሉ ከራያ እና አላማጣ የተፈናቀሉ ዜጎች ተናገሩ።

በህወሓት የሽብር ቡድን ወረራ እና ግፍ ምክንያት የተፈናቀሉ ከ28 ሺህ በላይ ዜጎች በሰሜን ወሎ ዞን ከድሬ ሮቃ በቅርብ ርቀት ላይ በሚገኘው ጃራ የስደተኞች መጠለያ ጣቢያ ይገኛሉ።

ከራያ ቆቦ፣ ራያ ባላ፣ ራያ አላማጣ፣ ከአላማጣ ከተማ አስተዳደር ፣ ከራያ አፍላ እና ዛታ አካባቢዎች የተፈናቀሉ ሲሆን ለበርካታ ወራት በችግር ላይ እንደሚገኙ ገልጸዋል።

በአሁኑ ሰዓት ከመንግሥት እና ከለጋሽ ድርጅቶች የተወሰነ ድጋፍ የሚደረግ ቢሆንም ከአካባቢው የአየር ንብረት እና አቀማመጥ አንፃር ሲታይ የዕለት ምግባቸውን ለማሟላት እንዳልቻሉ ይናገራሉ።

በወር 15 ኪሎ ግራም ስንዴ እና ሩብ ሊትር ዘይት በመንግሥት ይቀርባል ቢባልም፣ ይህም ወሩን ጠብቆ እየደረሳቸው እንዳልሆነ ለፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ተናግረዋል።

በመንግሥት ብቻ ሁሉን ነገር ለማሟላት አስቸጋሪ ነው የሚሉት ተፈናቃዮቹ፣ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ እና ድርጅቶች ትኩረት ሊሰጡን ይገባል ነው ያሉት።

ዘላቂ መፍትሄ እንዲመጣ እና ህዝቡ ከችግር እንዲወጣ እንደፍላጎታቸው ወደቀዬአቸው መመለስ ዋናው መፍትሄ መሆኑን ጠቁመው፣ በዚህ ረገድም መንግሥት አስፈላጊውን ጥረት ያድርግልን ሲሉ ጠይቀዋል።

በሰሜን ወሎ ዞን በተፈጠረው ችግር ከ500 ሺህ በላይ ተፈናቃዮች ነበሩ ያሉት የሰሜን ወሎ ዞን የምግብ ዋስትና ጽህፈት ቤት የቅድመ ማስጠንቀቂያ እና ምላሽ ባለሙያ አቶ አወል ሐሰን አብዛኛውን ተፈናቃይ ወደቀዬው መመለስ መቻሉን ተናግረዋል።በአሁኑ ሰዓት 51 ሺህ የሚሆኑ ተፈናቃዮች በዞኑ ውስጥ የሚገኙ ሲሆን፣ 30 ሺህ የሚሆኑት ብቻ በመጠለያ ካምፕ ይገኛሉ ብለዋል።

መንግሥት በመጠለያ ለሚገኙት ወገኖች የተለያዩ ድጋፎችን ሲያደርግ መቆየቱን ገልጸው፣ የሚሰጠው የድጋፍ መጠን ግን የተፈናቃዮችን ፍላጎት ማሟላት አልተቻለም ብለዋል።

ይህን ችግር ለመቅረፍም የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ የበኩላቸውን ሊወጡ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

ባለፉት 6 ወራት ሦስት ጊዜ መደበኛ ድጋፍ ለማድረግ የተሰራ ሲሆን፣ የስንዴ አቅርቦት የአካባቢውን ሥነ ምህዳር ያማከለ ባለመሆኑ ከሌሎች ክልሎች ተሞክሮ በመውሰድ ለ4ኛ ዙር ለመስጠት ታስቧል ነው ያሉት።

ዜና





አቶ እንዳለው መኮንን

# ተቋማት የአክሪዲቴሽን አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን እንደሚገባቸው ተጠቆመ

**ፍቃዱ ዴሬሳ**

አዲስ አበባ፡- ምርቶችና አገልግሎቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆኑና የተጀመረው የኢኮኖሚ እድገት ቀጣይነት እንዲኖረው ተቋማት በአክሪዲቴሽን አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን እንደሚገባቸው ተገለፀ።

"አክሪዲቴሽን፣ ለአካባቢ እና ለዘላቂ ኢኮኖሚ እድገት" በሚል መሪ ቃል የዓለም አክሪዲቴሽን ቀን እየተከበረ ነው። የኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን አገልግሎት ቀኑን በማስመልከት ከባለድርሻ አካላት ጋር በኢንተር ሌግዠሪ ሆቴል ውይይት አድርጓል።

በውይይቱ የተገኙት የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ እንዳለው መኮንን፣ የኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን አገልግሎት የተሰጠው ተልዕኮ ለተስማሚነት ምዘና ተቋማት ማለትም ለፍተሻ፣ ለህክምና ካሊብሬሽን ላብራቶሪዎች፣ ለኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን ተቋማት የአክሪዲቴሽን አገልግሎት መስጠት ነው። መንግሥት የአክሪዲቴሽን አገልግሎት በሀገር ውስጥ እንዲሰጥ ሲያደርግ ዜጎች የ3ኛ ወገን ብቃታቸው የተመሰከረላቸው አክሪዲት የሆኑ ተቋማትን የተለያየ የፍተሻ፣ የኢንስፔክሽንና የሰርተፊኬሽን ውጤቶች ተቀባይነትና ተአማኒነት እንዲያገኙ ለማድረግ ነው ብለዋል።

በዘንድሮው ዓለም አቀፍ የአክሪዲቴሽን ቀንም የዓለም ኢኮኖሚ በተመሰረተው ጤናማ ስነ ምህዳር ላይ ከፍተኛ ጫና በመድረሱ ስነ ምህዳሮች ተጠብቀው ለቀጣይ ትውልድ እንዲሸጋገሩ እንዲሁም በሀገር አቀፍ ደረጃ የተጀመረውን የአረንጓዴ ልማት አሻራ ለማሳካት ገንቢ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው አመልክተዋል።

ጥቂት ተቋማት ተቀባይነት ያለውና ተአማኒ የሆነ የተስማሚነት ምዘና አገልግሎት ለህብረተሰቡ እየሰጡ ቢሆንም በርካታ ተቋማት ግን ወደዚህ አገልግሎት አለመምጣታቸውን ገልፀው፣ ምርቶችና አገልግሎቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆኑና የተጀመረው የኢኮኖሚ እድገት ቀጣይነት እንዲኖረው ተቋማት በአክሪዲቴሽን አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን እንዳለባቸው ገልፀዋል።

የኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌትነት ጽጌመላክ በበኩላቸው ተቋሙ ምርትና የአገልግሎት ጥራቶችን ለማስጠበቅ ዓለምአቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ የላብራቶሪ አገልግሎቶች እንዲሁም ብቃት ባለው የሰው ኃይል አገልግሎቱን በመስጠት ምርትና ምርታማነትን ለማሻሻል እየሰራ መሆኑን አስታውቀዋል።

ተቋሙ የሚሰጣቸው የአክሪዲቴሽን አገልግሎቶች ዓለምአቀፍ ተቀባይነት ያላቸው ቢሆንም በሚፈለገው መጠን የአክሪዲቴሽን አገልግሎቶች ተጠቃሚ አይደሉም። አክሪዴት የሆኑ ተቋማትን በገበያው ተጠቃሚ የሚሆኑበት አሰራር በመፍጠር ሌሎች ተቋማት እንዲቀላቀሏቸውና ጤናማ የውድድር መንፈስ እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ገልጸዋል።

የሰው ልጅ የተፈጥሮ ሀብቶችን በመጠቀም ሂደት ውስጥ በብዝሃ ህይወትና ስነ-ምህዳሮች ላይ የሚያደርሰው ከፍተኛ ተፅዕኖ እንዲሁም የግሪን ሀውስ ጋዞች ልቀት መጨመር ለመቆጣጠር የተለያዩ ዓለምአቀፍ ደረጃዎችን፣ የአክሪዲቴሽንና የተስማሚነት ምዘና ተቋማት የጥራት አመራር ስርዓቶችን በመጠቀም በአካባቢ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት በመቀነስ ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገት ማምጣት እንደሚቻል ተናግረዋል።

ተቋሙ ላለፉት አሥር ዓመታት ለ35 ፍተሻ ላብራቶሪዎች፣ ለ50 የህክምና ላብራቶሪዎች ለዘጠኝ ኢንስፔክሽን ተቋማት እንዲሁም ለሁለት የሰርቲፊኬሽን ተቋማት በድምሩ ለ96 በውስን የአክሪዲቴሽን ወሰኖች አገልግሎት የሰጠ ሲሆን ለ35 ተቋማት የተሰጣቸው የአክሪዲቴሽን እውቅና መነሳቱን ከተቋሙ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

## "ኢትዮጵያና ሶማሊያ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ግንኙነት የበለጠ እንዲጠናከር በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል አስፈላጊው ጥረት እንደሚደረግም አረጋግጠዋል።

አዲሱ የሶማሊያ ፕሬዚዳንት ሀሰን ሼክ ማህሙድ ሥራቸው የተሳካ ይሆን ዘንድ ኢትዮጵያ አስፈላጊውን ትብብርና ድጋፍ እንደምታደርግም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አስታውቀዋል።

ኢትዮጵያና ሶማሊያ የሁለትዮሽ ግንኙነታቸውን ይበልጥ እንደሚያጠናክሩ ያላቸውን እምነት አመልክተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በዚሁ ንግግራቸው፣ ለፕሬዚዳንት ሀሰን ሼክ ማህሙድ የተሳካ የሥራ ዘመን እንዲሆንላቸው ተመኝተዋል።

ፕሬዚዳንት ሀሰን ሼክ ማህሙድ በበኩላቸው በኢኮኖሚ ጠንካራ እና ሰላሟ የተረጋገጠ ሶማሊያን ለመፍጠር እንሰራለን ብለዋል።

"ከአፍሪካ ቀንድ ሀገራትና ከመላው ዓለም ጋር ጠንካራ ትብብር እንመሰርታለን" ያሉት ፕሬዚዳንቱ፣ የትብብር መስኮችም ንግድ፣ ኢኮኖሚና ሽብርተኝነትን መዋጋት እንደሚሆንም መግለጻቸውን ኤፍቢሲ ዘግቧል።

## 44 ሚሊዮን ዜጎች በጤና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ጤና መድህን አገልግሎት አስታወቀ። ከጤና መድህን አገልግሎት ተጠቃሚዎች ሶስት ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር መሰብሰቡም ተገልጿል።

የኢትዮጵያ ጤና መድህን አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ፍሬህይወት አበበ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአገር አቀፍ ደረጃ ዜጎች 880 ወረዳዎች የሚገኙ 44 ሚሊዮን ዜጎችን በጤና መድህን አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል።

በሃገሪቱ በአሥራ ሶስት ወረዳዎች የተጀመረው የጤና መድህን አገልግሎት አሥራ አንድ ዓመት ያስቆጠረ ሲሆን፤ በአሁኑ ሰዓት 880 ወረዳዎች የሚገኙ 44 ሚሊዮን ዜጎችን ተጠቃሚ ማድረጉን ወይዘሮ ፍሬህይወት አመላክተዋል።

ወይዘሮ ፍሬህይወት በኢትዮጵያ ከሚገኙ ወረዳዎች መካከል 84 በመቶ በሚሆኑት ላይ አገልግሎቱን ተደራሽ ማድረግ መቻሉን ጠቅሰው፤ በዚህም ዘጠኝ ነጥብ አምስት ሚሊዮን እማወራና አባወራዎች ውስጥ የሚገኙ 44 ሚሊዮን የሚሆኑ ዜጎች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ሆነዋል ነው ያሉት።

ከጤና መድህን አገልግሎት ተጠቃሚዎች ሶስት ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር መሰብሰቡን ያመላከቱት ወይዘሮ ፍሬህይወት፤ ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀርም ከነበረው ሁለት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር ገቢ አንፃር ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ እድገት ማሳየት መቻሉን ተናግረዋል።

የጤና መድህን አገልግሎት አፈፃፀም በፍትሀዊ መንገድ መስተናገድን የሚመለከቱ ጥናቶችን መደረጋቸውን የገለጹት ወይዘሮ ፍሬህይወት፤ ሴቶች ህፃናት ያለምንም አይነት ተግዳሮት በመስተናገድ ላይ እንደሚገኙም ጥናቱ ማረጋገጡን ገልጸዋል።

በአባልነት ከተያዙት ዘጠኝ ነጥብ አምስት ሚሊዮን እማወራና አባወራዎች ውስጥ አንድ ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ያህሉ መዋጮውን መክፈል የማይችሉ እንደሆኑ የገለጹት ወይዘሮ ፍሬህይወት የሚገኙባቸው ወረዳዎች፣ ዞኖችና ክልላቸው መዋጮ ሸፍነውላቸው የአባልነት መታወቂያ እያወጡላቸው መስተናገዳቸውንም አመላክተዋል።

የፀጥታ ችግር በነበረባቸው አካባቢዎችም ጭምር የተሻለ አፈጻጸም እንዳለ ጠቁመው፤ ክፍተት በሚታይባቸው አካባቢዎች ያለውን አነስተኛ አፈፃጸም ለማሻሻልም ቀጣይነት ያለው ሥራ ይከናወናል ብለዋል።

## ‹‹የህወሓት አመራሮች ለመኖሪያ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አቶ መስፍን ለወጋህታ ጋዜጣ እንደተናገሩት፣ የህወሓት መሪዎች ከፖለቲካዊ ጥቅማቸው በስተቀር የትግራይን ህዝብ ጥቅም አስበው አያውቁም፤ በተለይም በዚህ ወቅት የአይደር ሪፈራል ሆስፒታል በነዳጅ እጥረት ምክንያት ለታካሚዎች አገልግሎት መስጠት አይችልም ማለታቸው ለህዝቡ ያላቸውን ንቀት የሚያሳይ ነው።

የነዳጅ እጥረት ሊኖር ይችላል፤ ነገር ግን በአይደር ሆስፒታል በርካታ ሰዎች በመብራት እጥረት ህክምና ማግኘት እየተሳናቸው የህወሓት አባላት በመኖሪያ ቤታቸው የመብራት አገልግሎት እንዳያገኙ መደረጉ የቡድኑ አባላት ለህዝቡ ደንታ እንደሌላቸው ነው የሚያሳየው ብለዋል።

አቶ መስፍን እንደሚሉት የነዳጅ እጥረት ቢኖርም ቅድሚያ የሚሰጠው ለመኖሪያ ቤት ሳይሆን ለህዝቡ ህይወት መሆን አለበት ብለዋል። በአንዳንድ ስግብግብ አካላት ምክንያት የተነሳ የነዳጅ እጥረት ሊኖር ይችላል፤ ነገር ግን የህወሓት አመራሮች በቤታቸው መብራት እያገኙ ሆስፒታሉ አገልግሎት መስጠት ማቆም የለበትም።

የህወሓት መሪዎች ከራሳቸው ጥቅምና ፍላጎት ውጪ በትግራይ ህዝብ ላይ የሚደርሰው ስቃይና መከራ እንደማያስጨንቃቸው የገለፁት አቶ መስፍን፤ የትግራይን ህዝብ ከፖለቲካዊ ጥቅማቸው አንፃር ስለሆነ የሚያዩት ህዝቡ ችግር ላይ መውደቁ ለፖለቲካዊ ጥቅማቸው እስካገለገለ ድረስ የህዝቡ ጉስቁልና የሚያሳስባቸው አይደሉም ሲሉ አቶ መስፍን ተናግረዋል።

የህወሓት መሪዎች ለትግራይ ህዝብ ንቀት አላቸው፤ ራሳቸው ምቹ ቦታ ላይ እየኖሩ ህዝቡን በውሸት ፕሮፓጋንዳ እንዲቸገርና እንዲሰቃይ አድርገውታል ብለዋል።

በአንደበታቸው ተቆርቋሪ እየመሰሉ ነው እየጎዱት ያሉት፤ በህዝቡ ስምና ድምፅ የሚነግዱ መሪዎች ናቸው፤ የትግራይ ህዝብ በውሸት ፕሮፓጋንዳ ተታሎ ብዙ ዋጋ ከመክፈል በስተቀር ምንም አይነት ጥቅም አግኝቶ አያውቅም ብለዋል።

ህወሓት የትግራይን ህዝብ ወዳጅ ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም ባለፉት 27 ዓመታት ሰላም፣ ዴሞክራሲ፣ ልማት፣ መልካም አስተዳደርና ፍትህ አላመጣለትም። ይልቁንም ከሌሎች ክልሎች በከፍተኛ ደረጃ ተጎድተዋል ሲሉ አብራርተዋል።

የትግራይ ህዝብ፣ ህወሓት ዋና ጠላቱ መሆኑን ሊያውቅ ይገባል፤ የስልጣን ዘመኑን ለማራዘም ሲል በውሸት ፕሮፓጋንዳ ሲያታልለው ቆይቷል። የቡድኑ አላማ ና ፍላጎት በእንደዚህ አይነት የውሸት ፕሮፓጋንዳ ለዘላለም መኖር በመሆኑ የትግራይ ህዝብ ይህንን ተረድቶ ቡድኑን በቃህ ሊለው ይገባል ብለዋል ።

በቅርቡ በመቀሌ የሚገኘው የህወሓት ቡድን ደጋፊ የሆነው ፍፁም ብርሃኔ በማህበራዊ ገፁ ላይ የአይደር ሪፈራል ሆስፒታል በነዳጅ እጦት ሥራ ቢያቆምም የህወሓት መሪዎች ቪላዎች ግን ሌሊቱን ሙሉ እየበሩ እንደሚያድሩ እና ይህ ተገቢ እንዳልሆነ በማህበራዊ ድህረ ገጹ ላይ ማስፈሩ ይታወሳል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የመንግስት የ2015 በጀት ዓመት ትኩረት የጀመርነው የልማት ጉዞ በተሻለ ፍጥነት የሚጓዝበትን ዕድል የሚፈጥር ነው!

መንግስት ሰሞኑን በኢኮኖሚ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሽዴ በኩሉ እንዳስታወቀው ለ2015 በጀት ዓመት ለመደበኛ ወጪ 345 ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር ፣ ለካፒታል ወጪ 218 ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር፤ ለክልል መንግሥታት ድጋፍ 209 ነጥብ አራት ቢሊዮን እንዲሁም ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ 14 ቢሊዮን ብር መቅረቡን አስታውቋል። በበጀት አመቱም የመንግስት ትኩረት ለዕዳ ክፍያ፣ ለሰብዓዊ ዕርዳታ፣ ለመልሶ ግንባታና ለሀገርን ደህንነት እንደሆነም አመልክቷል።

ሀገሪቱ በብዙ ተግዳሮት ውስጥ ባለችበት በዚህ ወቅት በረቂቅ ደረጃ የተያዘው የፌደራል መንግስት የ2015 ዓ/ም በጀት በአብዛኛው ሃገሪቱን እየተፈታተኑ ያሉ ችግሮችን መፍታትን ታሳቢ ያደረገ ነው። ለዚህ ደግሞ የበጀት ክፍፍሉም ሆነ የ2015 የመንግስት የትኩረት አቅጣጫ ጠቋሚ ነው።

እንደ ሀገር ለጀመርነው የልማት እንቅስቃሴ ስኬት ከሀገራትም ሆነ ከተለያዩ የፋይናንስ ተቋማት በብድር ያገኘነውን ገንዘብ በወቅቱ መክፈል ይጠበቅብናል።በዚህ በኩል እስካሁን ያለን አፈጻጸም የሚያበረታታ ነው። ይህንን እስጠብቆ መሄድ በአበዳሪዎች ዘንድ የነበረንን አመኔታ የሚያሳድገው ሲሆን ለተጨማሪ የብድር አቅርቦትም የተሻለ እድል የሚፈጥር ነው።

በዚህ በኩል ያለው የመንግስት ትኩረት ሀገሪቱ ለጀመረቻቸውና ለምታስባቸው ሚጋ ፕሮጀክቶች ፋይናንስ በማፈላለግ ሄደት ሊያጋጥም የሚችለውንም ተግዳሮት ሊቀንሰው እንደሚችል ይታመናል።ስለሆነም የሚበረታታ ነው ።

ከፍተኛ ቁጥር ያለው ዜጋ በሽብር እና በጽንፈኛ ቡድኖች ከቤት ንብረታቸው በተፈናቀሉበት ፤የመሰረተ ልማት አውታሮች በወደሙበትና በተዘረፉበት ተጨባጭ እውነታ ውስጥ መንግስት ለሰብአዊ እርዳታና መልሶ ግንባታ የሰጠው ትኩረት ዜጎች ካሉበት የማይመች ሁኔታ ፈጥነው ወጥተው ወደ ቀደመው ሕይወታቸው እንዲመለሱ የሚያስችል እንደሆነ ይታመናል። ይህ ደግሞ እነዚህ ወገኖቻችን ነገን በተሸለ ተስፋ እንዲጠብቁ የሚያደርግና ካሉበት የልብ ስብራት እንዲያገግሙ የሚያስችል ነው።

ከዚህም በላይ አሸባሪ ቡድኖች በግጭትና በጦርነት አካባቢዎች የፈጠሩትን ጠባሳ ቶሎ ፍቆ ህዝቡ ወደ ጀመረው ልማት ፊቱን እንዲያዞር የሚያስችል ነው።ታሪካዊ ጠላቶቻችንም ሆኑ የውስጥ ባንዳዎች ያሰቡትና ያቀዱትን ከዚያም አልፈው በተጨባጭ በተግባር ሊመነዝሩት ረጅም ርቀት የሄዱበትን የሕዝቡን ሕይወት የማጎሳቆል እኩይ ተልዕኮ ማክሸፍ የሚያስችል ጭምር ነው።

ያለንበት ወቅት እንደ ሀገር ከፍ ያሉ ተግዳሮቶች ውስጥ የምንገኝበት ነው።በአንድ በኩል በሀገር ውስጥ የሚገኙ አሻባሪ ቡድኖችና አክራሪ ሀይሎች በሌላ በኩል ደግሞ ታሪካዊ ጠላቶቻችንና የነሱ አይዞህ ባይ ኃይሎች የሀገርን ሕልውና በከፍተኘ ሁኔታ እየተፈታተኑ ያሉበት ነው።

ሀገርን ለማፍረስ እስከ ሲኦል እንወርዳለን ከሚለው አሻባሪው ሕወሓት ፤ በነጻነት ስም ነፃ አወጣዋለሁ የሚለውን ህዝብ ሳይቀር በመግደል የፖለቲካ ትርፍ የሚፈልገው የሸኔ ቡድንን ጨምሮ ጊዜና ሁኔታዎችን እየጠበቁ የህዝቡን ሰላምና መረጋጋት ከዚያም አልፈው ሀገረ መንግስቱን የሚፈታተኑ ኃይሎች ባሉበት ሀገር የተጀመረውን የለውጥ ጉዞ ለማስቀጠል አስተማማኝ ሰላም ማስፈን ወሳኝ ነው። ከዚህ አንጻር መንግስት የሀገርን ደህንነት ለማስጠበቅ ትኩረት መስጠቱ ለውጡን ለማስቀጠል ወሳኝ የሆነውን አቅም የመገንባት ተልእኮ አካል ነው።

በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ካለው ተለዋዋጭ ፖለቲካም ሆነ በአካባቢው ላይ ካለው ዓለም አቀፍ ትኩረት አንጻርም ቢሆን ሀገሪቱን ከውስጥም ከውጪም ደህንነቷን አስተማማኝ ማድረግ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ አሁን ትልቁ ሀገራዊ አጀንዳ ሊሆን ይገባል። የሀገሪቱንም ብሄራዊ ጥቅም ለማስከበር ከሚኖረው ፋይዳ አንጻር መንግስት ለሀገር ደህንነት የሰጠው ትኩረት የሚበረታታ ነው።

ዘላቂ ሀገራዊ ሰላምና መረጋጋት ለማምጣት ወሳኝ አቅም ፤ሀገረ መንግስቱን በጠንካራ መሰረትና አቅም ላይ እንዲገነባ የሚያስችለው፤በጠንካራ የቁጥጥር ስርአትና ዲሲፕሊን ከተመራ የጀመርነው የልማት ጉዞ ወደ መስመሩ ተመልሶ በተሻለ ፍጥነት የሚጓዝበትን እድል የሚፈጥር ነው!


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## ገሃድ የወጣው አፈና!

**በእምነት**

አሸባሪው ሕወሓት መራሹ ችግር ፈጣሪ ቡድን እንደ አገር ጦርነት አውጆብን ሁሉ ነገር ወደ ጦር ሜዳ ከሆነ አመታት እየተቆጠሩ ነው። በእነዚህ ጊዜያት ውስጥ ኢትዮጵያ እንደ አገር ሃብት ንብረቷን ከማጣቷ፣ የጀመረችውን ልማት ከማስተጓጎሏ ባሻገር አምራች የሆነውን ወጣት ሀይሏን እንዲሁም ሌላውን ዜጋዋን ለመገበር የተገደደችበት ወቅት ሆኗል።

ለህዝብ ጥቅም ቆሜያለሁ በሚል የውሸት ብሮፖጋንዳ ያጣውን ስልጣን መልሶ ለማግኘት ቆሜለታለሁ የሚለውን ህዝብ እያፈነና እያሰቃየ ያለው ሕወሓትም ዛሬም የጥፋት ድግሱን እየደገሰ ስለመሆኑ የአደባባ ሚስጥር ከሆነ ውሎ አድሯል ። ከጥፋት ድግሱ ተጠቃሚ የሚሆነውም ማን እንደሆነ የተሰወረ ጉዳይ አይደለም ።

ዛሬ ላይ በትግራይ ትልልቅ ከተሞች ውስጥ ህዝብ እንደጉድ እየታፈሱ ወታደራዊ ስልጠናን እንዲወስድ ይደረጋል፤ ልጄን አልሰጥም ያሉ ወላጆች በአገራቸው ላይ መሆናቸውን እስኪጠራጠሩ ድረስ ከፍተኛ የሆነ እንግልትና ስቃይ እየደረሰባቸው ስለመሆኑ ተደጋግሞ እየተነገረ ነው። ባስ ሲልም ሰዎች ያለምንም ምክንያት ጎዳናዎች ላይ ህይወታቸው እንዲጠፋ እየተደረገ ነው። ይህ የወንበዴ ቡድን ይህን ሁሉ የሚያደርገው እንደሚለው እውነት ለትግራይ ህዝብ ነው? መልስና ፍርዱን ለእናንተ እተወዋለሁ።

ህዝባዊ ወያኔ ሀርነት ትግራይ ከዚህ ቀደም ማለትም የትጥቅ ትግል ብሎ በጀመረበት ጊዜ በርካታ የትግራይ ወጣቶችን ገብሯል። በዚህ ጊዜ ልጆቹን ያጣው የትግራይ ህዝብ ገና ቁስሉ አልጠገገለትም፤ እንባው አልደረቀም፤ ነገር ግን ዛሬም ለሌላ እልቂት ልጆችህን አምጣ እየተባለ ነው።

ይህ ቡድን መደበቂያ ሲያጣ ከመሃል አገር ፈርጥጦ የትግራይን ህዝብ እንደጠቀመ በማስመሰል ጉያው ተወትፎ ያልበላውን እያስተፋው ከእህት ወንድሞቹ ጋር ደም እያቃባው ነው። ቡድኑ ምን ጊዜም ከራስ ወዳድነቱ ወጥቶ ከጥፋቱ ተምሮ ህዝብን ለመካስ አገርን ዳግም እንድታንሰራራ ለማድረግ አንዳችም ሃሳብም እቅድም የለውም፤ ምክንያቱም እሱ ስልጣን ላይ ካልወጣ አገር ለእሱ ምንም ስላልሆነች ።

> የሕወሓት የፍትህ ችግር እስከ ዛሬም ህዝቡን ሲያደቅ ነበር ዛሬም ህዝቡ ፍትህ ተጓሎበት የመኖሩ እጣ ፈንታ ጥያቄ ውስጥ ወድቋል ። እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ይህንን ሁሉ በደል በህዝቦች ላይ የሚያዘንበው ሕወሓት ቡድን እንጂ አምላክ አይደለም እንደ ማንኛውም ፓርቲ በአንድ ወቅት አገር ሲያስተዳድር የነበረ በህዝብ ጥያቄ መሰረት ደግሞ ከመንበረ ስልጣኑ የተባረረ ተራ ቡድን ነው

አሁን የትግራይ ህዝብ በአመፅ፣ በጭቆናና በአሸባሪነት የልጆቹን ህይወትና ለአመታት ደክሞ ያፈራውን ንብረት እየተነጠቀ ነው። ለዓመታት የዘለቀው ከባድ በደል፣ ወንጀልና አፈና ዛሬም ተጠናክሮ በመቀጠል ህዝብ ሌላ ስቃይ ውስጥ እንዲገባ እየሆነ ነው ።

ከዚህ በተጨማሪም የትግራይ ህዝብ ወገኑ የሆነው ሌላው ህዝብ የላከለትን ምግብ ፣ መድሃኒት፣ የህክምና ቁሳቁስ እንዲሁም ለልጆቹ የሚመግበውን አልሚ ምግብ በጠቅላላው የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ እንዳያገኝ በማድረግ ረሃብና ሰቆቃን እንደ ጦር መሳሪያ እየተጠቀመ ያለ አመጸኛ ቡድን ሆኗል ።

የሕወሓት የፍትህ ችግር እስከ ዛሬም ህዝቡን ሲያደቅ ነበር ዛሬም ህዝቡ ፍትህ ተጓሎበት የመኖሩ እጣ ፈንታ ጥያቄ ውስጥ ወድቋል ። እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ይህንን ሁሉ በደል በህዝቦች ላይ የሚያዘንበው ሕወሓት ቡድን እንጂ አምላክ አይደለም እንደ ማንኛውም ፓርቲ በአንድ ወቅት አገር ሲያስተዳድር የነበረ በህዝብ ጥያቄ መሰረት ደግሞ ከመንበረ ስልጣኑ የተባረረ ተራ ቡድን ነው። ታዲያ ይህ ቡድን ህዝቡን እንደ ህዝብ በልቶ ከመጨረሱ በፊት እልባት መስጠት የትግራይ ህዝብ የተሳነው ለምን ይሆን?

ይህ ቡድን በሰላም መኖር የማይችል ሁከትን ብጥብጥ የህልውናው መሰረት ነው ።ይህንንም እኛ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳንሆን መላው ዓለም በተጨባጭ የሚያውቀውና የሚረዳው ነው ፤ ታዲያ ምነው መፍትሔው ራቀ? የእኔ ብቻ ሳይሆን የብዙዎቻችን ጥያቄ ነው።

አሁን ላይ የትግራይ ህዝብ ልጆቹን ከእልዕቂት ሊታደግ ይገባል። ህዝብም በቃህ ከላዬ ላይ ውረድ ማለት መቻል አለበት። ይህ ምናልባት ከሕወሓት መሰሪ አካሄድ አንጻር ቀላል ላይሆን ይችላል ። “ነገር ግን ድር ቢያብር........! ነውና ህዝብ እንደ አንድ ሆኖ ከተነሳና ካበረ የሚያቅተው ነገር ስለሌለ በአንድ መነሳቱ የዘመናት ጠላቱ የሆነውን ይህንን አሸባሪ ቡድን ከላዩ ላይ አውርዶ ለመጣል መንገድ የሚሆነው ይመስለኛል።

በሌላ በኩልም በተመቸ ኑሮና በነጻነት እየኖረ ያለው የትግራይ ዲያስፖራም ስለ አያቶቹ ፣ እናቶቹ እህት ወንድሞቹ ብሎ ከገባበት አጉል መንገድና አስተሳሰብ በመውጣት እንዲሁም ምን እየሰራሁ ነው? በማለት ቆም ብሎ ሊያስብና ከህሊናው ጋር ተታርቆ ከወገኑ ጎን ሊቆም ይገባል።

ይህንን በማድረግ እንደ አምላክ ተፈርቶ ወይንም ደግሞ በህዝብ ላይ ፈላጭ ቆራጭጥ ሆኖ ለያዥ ለገላጋይ ያስቸገረውን የወንበዴ ስብስብ ከሁላችንም ላይ ማውረድ በቃህ ማለት እንደ ህዝብ ተሰባስበንና ተረባርበን አገራችንን በማሳደግ አገሮች የደረሱበት ደረጃ መድረስ እኛም እንደሌሎቹ ጠግበን መብላት፣ ተርፎን ማበደር ልጆቻችንን አስተምረን ለአገር ለወገን የሚተርፉ ማድረግ በጠቅላላው ኢትዮጲያን የቀደመ ገናናነቷ እንዲመለስ ማድረግ አለብን ። አበቃሁ!

## ነፃ ሃሳብ

# ተምሳሌት የሚሆኑን

# ኤሊት፣ ልሂቃን፣ አክቲቪስትና ምሁራን ያስፈልጉናል

**መኩሪያ አለማየሁ**

ሀገሪቱን ከፊትም ከኋላም በበጎም በክፉም ለመምራት ፖለቲካውን በመግዛትም በመቃወምም የሚዘውሩት ግንባር ቀደም ባለድርሻዎች ኤሊቶች፣ ሊሕቃን፣ አክቲቪስቶችና ምሑራን ናቸው። የእነዚህ መገኛ የት ይሆን ካልን በግለሰብ፣ በቡድን፣ በተቋም፣ በድርጅት እንዲሁም በአማራጭና በገዢ መንግሥት ውስጥ እናገኛቸዋለን። ከዚህ በታች ለሚቀርበው ጽሑፍ ኤሊት፣ ልሒቅ፣ አክቲቪስትና ምሁር በየአንቀጹ በተደጋጋሚ ለአጽንዖት ስለሚቀርብ አንባቢን ላለማሰልቸት ከስሞቻቸው የመጀመሪያውን ሆሄ በመውሰድ ኤሊአም በሚል ስያሜ ለመጠቀም ወደድኩ።

**ጁሊየን ቤንዳ**

ምሑራን በሀገራዊ ድንበርና በጎሳ ማንነት በማይገደብ ዩኒቨርስ ውስጥ የሚኖሩ ናቸው።

መሠረታዊ ሰብዓዊ ፍትሕን በሚመለከት የምትሟገቱ መሆን አለባችሁ። የእናንተ ሀገር ሲሆን ብቻ እየመረጣችሁ የምትሟገቱ ከሆነ የምሑርነትን ነፍስ ታጣላችሁ። መሠረታዊ ችግር ያለው የራስን ማንነት፣ ባሕል፣ ኅብረተሰብና ታሪክ ከሌሎች ማንነቶች ታሪክና ሕዝብ ጋር ለማስታረቅ መቻል ነው።

**ፕ.ር ሰይድ**

ኢትዮጵያ ከስጋ ዐይናችን በላይ ናት። በንሥር ዐይን የምትነጸር ረቂቅ ሀገር ናት። ናላ ከሰማይ ይሰፋል እንዲሉ እሷን ለማሰብ ሰፊ ሕሊና ግድ ይላል። እፍኝ በምታክል ልባችንም አትመረመርም። በዘመን ብዙ፣ በታሪክ ሰፊ፣ በተፈጥሮ ሀብት በውድ ስጦታ የታደለች ዓለም በተለየ ሁኔታ የሚያያት ልዩ ሀገር ናት።

ይህችን ውድ አገር ለመታደግ ኤሊአም ኃላፊነታችሁ የጎላ ነው። ለአገር ዕድገት፣ ሰላም፣ ብልጽግና ከመድረክ ጀርባ፣ ከጫወታው ሜዳ ዳር፣ ከቀዘፋው ውጪ፣ ከባሕሩ አፋፍ ላይ ትሆኑ ዘንድ አልተጠራችሁም። ሀገር በመገንባት ሂደትም ዜጋው የሥራው አካል እንዲሆንና የድርሻውን እንዲያበረክት እንደ አንድ የተሳካ ተውኔት በጋራ በመጫወት፣ በጋራ በመድመቅ የክብርን ፍሬ ለማሳየት ሀገርን መድረክ ዓለምን ተመልካች አድርጋችሁ የምትጋበዙበት ዕድል መፍጠር የምትችሉት እናንተ ናችሁ።

በተለይም በሀገር ግንባታ ላይ ሰፊ ድርሻ ያላችሁ የመንግሥት ሥራ አስፈጻሚ፣ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ሕዝባዊ ተቋማት ውስጥ ያላችሁ፣ መምህራን፣ ጋዜጠኞች፣ ደራሲንና የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች ሚዛን የደፋ ድርሻ ይጠበቅባችኋል። ለዚሕ " የሰጎን ፖለቲካ" አስተሳሰብን ወደዳር ማድረግ ይገባል። ከዚሕ አንጻርም በሚገጥሙ ተግዳሮቶች ተሸንፎ ወደኋላ ሳይባል፣ የዛሬ ድኅነቷን ሽሮ በሁለገብ የበለጸገች ሆና ለነገም የምትተርፍ ሀገር ለመገንባት ዕድሉ በእጃችሁ ነው።

ሀገርን የሚቀይሩ ጥቂት ግለሰቦች ናቸው። ዓለምን እንኳን በአንድ ጣት የሚቆጠሩ የበራላቸው ሰዎች ናቸው የቀየሯት። ዓለም መልካም ሰዎች ቁጥራቸው ይነስ እንጂ ነጥፈውባት አታውቅም ይባል የለ። ኤሊአሞች አርቆ አስተዋዮች፣ ለሰው ኖረው፣ ለሰው ሠርተው፣ አገርን ለመለወጥ በሐቀኝነትና በንጹሕ ልብ ደፋ ቀና የሚሉ ናቸው። ባነቁት ሐሳብ፣ በቀመሩት ቀመር፣ በዘረጉት ሥርዓት ሀገርን ይለውጣሉ።

ዛሬ አገር በፊደል ምሑርና በልቡም ቅን የሆነ ኤሊአም ትፈልጋለች። የተማረ፣ በጎ ሐሳብና ቅን ኤሊአም የግል ፍላጎቱን፣ ብሔርተኝነቱንና ጎሰኝነቱን ጥሎ ሁሉም ነገር ከአገር በኋላ የሚልበትን ወኔ አንግቦ የሥራውም ፍሬ በዚህ የሚለካ ሊሆን ይገባል “”””””። በአገራችን ጉዳይ ብዙ የሚቆጩ ነገሮች አሉ። ደግሞ ሁሉም ሰው በዕውቀቱ፣ በጊዜው በጉልበቱ፣ በክህሎቱና በገንዘቡ እንደተለገሰው በሀገር ላይ እንዳለመጠቀም የሚቆጭ ነገር አይኖርም። ሕልምን ለማሳካት፣ ቁጭትን ለመወጣት፣ ጥማትን ለማርካት... የሀገርን ዕድገት፣ ሰላሟ ተጠብቆ፣ ፍትሕና ዲሞክራሲ ሰፍኖ ልትታይ የምትፈለገውን ሀገር በባዶ አትመጣም በጠንካራ ጥረትና ድካም እንጂ።

ጠንካሮች አርቆ አስተዋዮች ሀገርን ይፈጥራሉ። በየትኛውም አገር ሁሉም የታሪክ ክስተቶች በሰው የተፈጠሩ ናቸው። ሀገር በጥረት እንዲገነባ እስራኤል ምስክር ነች። ለብዙ ብዙ ዘመናት ፈርሰው፣ እንደጨው ተበትነው፣ አባቶቻቸው ከተወለዱበት ቀዬ ለቀው፣ ዘራቸውን በሰው አገር ቀጥለው ይኖሩ ነበር። ነገር ግን በጭንቅላትና በልባቸው ውስጥ ያልፈረሰችው አገራቸውን ዳግም ትንሳኤ ሰጥተው ዛሬ የዓለም ቁንጮ አድርገዋታል።

**በኢትዮጵያ ምድር የሰባት፣ የአምስት እንበለው የሦስት ሺህ ገናና ታሪክ ውስጥ ጥቂት ዘመን ብቻ ወደ ኋላ ብንሄድ ተበታትና የኖረችበት ዘመን የቅርባችን ነው። በዘመነ መሳፍንት ዘመን ከትርፍ ይልቅ ኪሳራ፣ ከፍቅር ይልቅ ጥላቻ፣ ከሰላም ይልቅ ጦርነት ከኅብረት ይልቅ መበታተን በመንገሡ የጨለማው ዘመን ተብሎ ተሰይሟል**

እስራኤላውያን በየሀገሩ እጅግ የሚዘገንን አስከፊ ዘመናትን ተስፋ ከሚያስቆርጥ ሁኔታ ጋር ተጋፍጠዋል። ፍላጎት ካለ፣ ሕልም ካለ በረሃን ገነት ማድረግ ይቻላል። የተበተነውን መሰብሰብ፣ ያልተማረውን ማስተማር፣ የተራበውን ማብላት፣ የተጠማውን ማጠጣት፣ የታረዘውን ማልበስ፣ መጠጊያ ያጣውን ባለቤት ማድረግ፣ ጎዳና የወደቀውን ማንሳት፣ ነዳያንን መርዳት.... ይቻላል። የጠፋው ቅን ልብ፣ በጎ ሐሳቢና መልካም ሕሊና ያለው ኤሊአም ነው።

በሀገራችን ላይ የፍቅር፣ የሰላም፣ የዕድገትና የአንድነት አየር ለማስተንፈስ የችግሯን ሰንኮፍ መንግሎ የሚጥል የበራላቸው የሚፈለጉበት ጊዜው ዛሬ ነው። ዛሬ ለሀገራችን የሚያስፈልጋት በድርሰቱ ልዕልናችንንና አንድነታችንን የሚጻፍበት፣ የታፈነ ዜማ ነጻ ወጥቶ የሕዝብ ልብ የሚያዜምበት፣ በጠቢባን የተሻለ ምስጢር የሚገለጥበት፣ ያላሰብንበትን አጎዝ ሐሳብ የሚቀመርበት፣ የተዳፈነው ሐሳብ ተገልጦ ቅኔ የሚዘረፍበት፣ ሰዓሊያን በተወደሩ ሸራዎቻቸውና በተለወሱ ቀለሞቻቸው የጋራ ምስል፣ የጋራ ገጽታ፣ የጋራ ድምቀት የሚሸከፉበት፣ በየቤተ ተውኔቱ ኅብር እሴት፣ ኅብር ታሪክ፣ ኅብር ሃይማኖት የአንዲት ትልቅ ሀገር የሚመደረክበት ዐውድ በሁሉም የኪነ ጥበብ ዘሮች የጋራ ሀገራዊ መገለጫዎች የሚታይበት እንጂ የምትነቃቀፍበት ጠይመን የምንታይበት“ በአሉታ ብቻ የምንሰለፍበት ሊሆን አይገባም።

ዛሬ እንደሌሎቹ የአደጉ ሀገራት ጥበባትን ለሰው ሀብት ለመገንባት ልንጠቀምበት ይገባል። ሕዝብንና ሀገርን ለመምራት በቅን ልብ፣ በብዕሩ አዕምሮ መዘጋጀትና መብቃት ይፈልጋል። የትናንቷና ገናና ትልቋን ሀገር ወደትልቅነቷ ለመመለስ ከሞቀ ደም ይልቅ ሰፊ ጥበብና ጥልቅ የሀገር ፍቅርን ይዞ መገኘት ግድ ይላል። እርስ በእርስ በመናከስ፣ አንድ ጥግ ላይ ቆሞ የጎሳ ፍላጻ በመወርወር ሰላምን፣ አንድነትና ብልጽግናን ማምጣት አይቻልም። እንደሰላም ማትረፊያ እንደጥላቻ ደግሞ ክፉ ጦርነት የለምና በዚህ አሚነ መሠረት በመታነጽ ዛሬን በአግባቡ ተኑሮ የነገን ፍሬ፣ ዕድልና ተስፋን ለሕዝብ ማሳየት የሚችል ባለቅን ልቦናዎችና ባለብሩህ አዕምሮዎች የሆኑ መንገድ ታላሚ ኤሊአም አገር በስስት ትፈልጋለች።

በኢትዮጵያ ምድር የሰባት፣ የአምስት እንበለው የሦስት ሺህ ገናና ታሪክ ውስጥ ጥቂት ዘመን ብቻ ወደ ኋላ ብንሄድ ተበታትና የኖረችበት ዘመን የቅርባችን ነው። በዘመነ መሳፍንት ዘመን ከትርፍ ይልቅ ኪሳራ፣ ከፍቅር ይልቅ ጥላቻ፣ ከሰላም ይልቅ ጦርነት ከኅብረት ይልቅ መበታተን በመንገሡ የጨለማው ዘመን ተብሎ ተሰይሟል። ዛሬም ዓላማና ግቡ መለያየት በመናፈቅ እኔነትን ብቻ ካቀነቀንን የተያያዝነው ፖለቲካችን ዳግማዊ ዘመነ መሳፍንት ልደቱን ያፋጥንብናል።

ዛሬ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ቆም ብሎ የሚያስብበት ጊዜ ነው። አንዱ የአንዱ ቁስል ሊነዝረው የሚገባበት ጊዜም ነው። ያለመሰልጠናችንና ያለመበልጸጋችን ምክንያት ልንፈትሽ ይገባል። ዛሬ በሥራ ፍሬአቸው የተገለጡ፣ የሕዝብ አፍ ሆነው የልቡን አውቀው የሚያርስ መልስ የሚመልስለትን ልብ ያለው ኤሊአም በብዛት ይፈለጋል። የዜጋውን ተብሰልስሎት የተጋሩ፣ አርቆ አሳቢዎች ኤሊአም መበርከት አለባቸው። በኢትዮጵያ ፍጹም ሰላም በማምጣት ድኅነትን ኋላቀርነትን፣ ጉስቅልናን እንደእርስት የዜጋው ቅጽል ሊሆን አይገባም የሚሉ፣ በአገሪቱ ላይ ድሃ ተበደለ ፍርድ ተጓደለ በማለት የተንሸዋረረውን ሥርዓት መስመር የሚያሲዙ ኤሊቶች ያስፈልጉናል።

**ይህቺ ትልቅ ዋርካ፣**

**ይህቺ ትልቅ ሾላ፣**

**በገለባ ቀረች ፍሬዎቿን ጥላ። መላኩ ጌታቸው**

ተብሎ ስንኝ በተቋጠረላት ሀገር በኩር ፍሬ ሆኖ የዋርካዋን በለስና አበባ ሊመልሱ፣ ስር ሰደው ሊያለመልሙ፣ በቅን ሐሳብ በትሑት ልብ በአፍቅሮተ ሕዝብ ድጋፍና ይሁንታን አንግበው፣ ሀገር ሊመሩ የሙሴን አሰረ ፍኖት ይዘው ሕዝብን ከካራን ወደከነዓን ሊመልሱ የሚችሉ የሕዝብን ልብ የሚያሳርፉ ኤሊአም ያስፈልጋሉ። እንዲህ ሲሆን በአጭር ጊዜ ስኬትና ብልጽግናም ይመጣል። ሕልምም በበጎ ይፈታል። ነገም በጥሩ ይፈኩራል። ዛሬ የኢትዮጵያ ስኬት፣ ብልጽግና“ የሰላሟ ባንዲራ የሚውለበለብበት ሰማይ ሁሉም ይናፍቃል። ለዚህም በኤሊአሞቻችን ልብና መንፈስ ውስጥ ለሀገር የሚተርፍ መልካምና ቅን ሐሳብ ሲኖር ብቻ ነው። ይህን ሐሳብ አርክቴክት አሐዱ በላይ አድምቆ ያፀናዋል።

አንድ የእምነት ፍልስፍና ላንሳልህ፣ ጥሩ ነገሮች ምንጭ አላቸው። ፀሐይ ምንጭ አላት። ጨለማ ግን ምንጭ የለውም። የብርሃን አለመኖር ነው የሚፈጥረው። ጨለማን ይዘህ እዚህ ክፍል ውስጥ መግባት አትችልም። ፀሐይ እንዳትገባ ካደረክ ወዲያው ጨለማ ትፈጥራለህ። ጥሩ ነገሮች ምንጭ አላቸው። መሐይምነትን የዕውቀት አለመኖር ነው የሚፈጥረው። ለአንድ ሰው መሐይምነትን ልትሰጠው አትችልም። ዕውቀት ካልሰጠኸው መሐይም ነው። ሀብት እንጂ ድኅነትን ልትሰጥ አትችልም። ፍቅር፣ ቸርነት፣ ታማኝነት ምንጭ አላቸው። ምንጫቸውም እግዚአብሔር ነው። እነዚህን ነገሮች ነፍሳችን ታዳብራለች። የምታደርገውም መልካሙን ነገር ነው። መጥፎው ነገር በጥሩ አለመኖር ነው የሚመጣው።

ለሀገር መልካም መልካሙን ብርሃን ብርሃኑን በመስጠትና በመሥራት የሀገርንና የሕዝብን ሕይወት ማቅናት ይቻላል። ከዛሬ 100 ዓመት በፊት የነበሩ በሙያቸው ሐኪም ቢሆኑም በአጭር የሕይወት ስንቃቸው፣ በሰፊ የንባብ ልምዳቸው፣ በተቀባ የሥነ ጽሑፍ ፀጋቸው ቅርስ የሆነ ጥበብ ፍሬ በመጽሐፋቸው ጥለው ያለፉት ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ እንዲህ ብለው ነበር። ምስኪኗ ኢትዮጵያ ሆይ የዕድልሽ በር መቼ ይነጋ ይሆን? ይህ ትንቢታዊ ንግግር የመሰለው ሐሳባቸው እውን ሆኖ ኢትዮጵያ ምስኪን ሆና የዕድሏ በር ሳይነጋና ሳይከፈት ለባዕዳን እጇን እንደዘረጋች ከምጽዋት ሳትወጣና የተረጋጋ ሰላም ሳይሰፍንባት በጦርነት፣ በኢ-ዲሞክራሲያዊነት፣ በኢ-ፍትሐዊነትና ሰላም በማጣት የዳኅሰ ሰነድ ሰንዳ አንድ ክፍለ ዘመን በላይ አልቦ ኤሊአም ሆና ተጉዛለች።

የሀገርን ዕድገትና ብልጽግናን ሽተው በለመለመ ታሪክ የተሠራው ሕዝብ ዳዋ ሊውጠው ሲዳዳ በቅንነት መርተው ከወደቀችበት ሊያነሷት፣ የጨለማ መንጠላይቷን ሊገፉላት፣ ስብራቷን ሊጠግኑላት፣ ተስፋዋን የሚመልሱላት፣ የልቧን መሻት የሚፈጽሙላት፣ ሕዝብ አክባሪ፣ በሕዝብ ልብ የሚነግሱ፣ ከሕዝብ ወጥቶ ሕዝቡን የሚዋጁ ኤሊአም ለኢትዮጵያ እንደሚያስፈልጋት ዶ/ር ምሕረት ደበበ ከሥነ ባሕሪ ሐኪምነቱ በተጓዳኝ ከያኒነቱን ተጠቅሞ በጥበብ ብዕሩ እንዲህ ብሏል።

**....ወደሕዝብህ ተመለስ፣ ወደሀገርህ ግባ፣ የቆሰለውን የሀገሪቷን ነፍስ እያከማችሁ፣ የተፈረካከሰው ኢትዮጵያ ክብርና ማንነት ፈልጋችሁ ከወደቀበት አንሱት፣ የዚህን ምስኪን ሕዝብ ፍርሃቱና ድንጋጤውን አርግቡለት፣ ጥላቻውንና አለመተማመኑን፣ ጭካኔውና ስግብግብነት .... የበሽታ ምልክቶቹ ናቸው እንጂ የጤነኛ ሰው፣ የሰለጠነ ሰው ኅብረተሰብ ባሕሪያት አይደሉም። አለመደማመጥ፣ ልዩነት፣ መፍራት በኩራት ተውጠው የበታችነት ስሜት መሰቃየት ሌላውን ጥሎ ትልቅ ለመሆን መሞከር ኹሉ የተሸነፈ ማንነት፣ የዘቀጠና የተቀጠቀጠ ሰብዕና መገለጫዎች ናቸው።**

ሕዝብ የመረጣቸው፣ በስራ ፍሬ ለውጥን የሚያሳዩ፣ ሀገሪቷ ከተኛችበት ሊቀሰቅሷት፣ ካጎነበሰችበት ሊያቀኗት፣ ከተበታተነችበት ሊሰበስቧት፣ ሥልጣኔዋን ሊመልሱላት፣ ተስፋዋን ሊሰጧት፣ ዳግማዊ የብልጽግናና የሥልጣኔ ትንሳኤዋን ሊያውጁ በሥልጣን ሳይሆን በሥራ፣ ሀገር ሊያገለግሉ የጠየመ ታሪኳን ለማደስ፣ በአዲስ ተስፋ፣ በአዲስ ፍቅር ሕዝብን ደምሮ አንድ ሀገርና ትልቅ ኃይል ያላት ኃያል አገር የሚፈጥሩ ኤሊአም ናቸው።

በንጽሕና፣ በፍቅርና በታማኝነት የሚከወን ነገር ተከታይ ያፈራል። መልካም ዜጋን ይፈጥራል። አስተዋይ ሕዝብ ይሠራል። በዕውቀትና በመረጃ ብቻ ሕዝብና ሀገር አይገነባም። በሰላም፣ በፍቅርና በቅንነትም መዋጀት ግድ ይላል። ለብዙ ጊዜያት አርአያ የሚሆነን ያጣነው የፍቅር ባንዲራ፣ የሰላም ዝማሬ፣ የዕድገት መም፣ የሥልጣኔን ፋና.... ከቅን ልብ ነቅቶ የሚያጎናጽፉንና የሚያመላክቱን በማጣት ነው። ዘመናትን በፈጀው ልማት ችግር አልተፈታም። እውነተኛ ይቅርታ አልመጣም። በጎጥ በስደት፣ በጠላትነት የተፈረጁትን በክብ ጠረጴዛ ክብ ልብ አስፈጥሮ ፍጹም የፍቅር ጽዋን አላስጎነጨም። ለዕድገትና ለብልጽግና በፍቅርና በጋራ መኖር ኪሳራ የሌለው ልዩ ትርፍ ነው።

የራስ በራስ ጥላቻና መለያየት ውጤቱ ቀላል አይደለም። ከድንበር ባሻገር ያለ ጠላት ልኩን፣ ጊዜውን፣ ጉዳትና ጥቅሙ ይታወቃል። ቶሎም መፍትሔ ይሰጥበታል። የራስ በራስ ጠላትነትና መጠላላት ግን ትርፍና አሸናፊነት የሌለው ዝቅጠት ነው። የውስጥ መነቋቆር እንደተዳፈነ ረመጥ ነው። ለዐይን ጎልቶ ሳይታይ ሲቀር የሌለ ይመስላል እንጂ ውስጥ ውስጡን ትውልድ ይፈጃል። ጠፍቶ አይቀርም፣ በትንሹም በትልቁም ትንፋሽ ይቀጣጠላል። ሲነድ አገር ይፈጃል። ደግሞ በረደ፣ ጠፋ ሲሉት በጥቂት ጭረት ከአንዱ ጫፍ ብቅ ይላል። አንዳንዴም ጭካኔው ለጠላት ከተሰበቀው ጦር ይብሳል። በሁለት ወገን እንደተሳለ ሰይፍ ፈጥኖ መትሮ ይፈጃል።

በመልካም ሀገር ገንቢዎች ጥሩ ታሪክ ሰርቶ መልካም ስም ማትረፍ ሽጋ ነው። ከየትኛውም ዜጋ በላይ መማር፣ ማሰብ፣ ትልቅ ደረጃ መድረስ ውጤቱ መሆን የአለበት በተማሩበት የሙያ መስክ፣ በተቆናጠጡት ሥልጣን ጉልበትን፣ ጊዜን፣ ዕውቀትን፣ ክህሎትንና የተፈጥሮ ሀብትን በማስተባበር ዳር ቆሞ ከተመልካችነትና ቅንብብ ካለ ጎሰኝነት ተወጥቶ ለታሪካዊቷና ታላቅ ሀገር አንዲት ጡብ ለማበርከት መጣር ከምንም የበለጠ ታላቅነት ነው።

ከኤሊአም የአደገችና የበለጸገች ሀገር ለመገንባት አዲስና ልዩ የጋራ ርዕዮት በማዘጋጀት ትልቋን ኢትዮጵያ ዳግም ትንሳኤዋን ትመልሱ ዘንድ የሀገሪቷ ዕጣ ፈንታ በእጃችሁ ነው። ሀገር በጥቂት ንጹሓንና አገር ወዳድ አዋቂዎች ልትገነባ ትችላለች። ጋሽ ስዩም ተፈራ እንዳሉት ዓለም በሥልጣኔዋ እዚህ የደረሰችው ምክንያት ያላቸው ሰዎች ስለተፈጠሩ ነው። ከኤሊአም በላይ በጥሩ ምክንያትና ዓላማ ማን ይኑር ማን አገር ይፍጠር በተለይ ዛሬ ሀገር ለመለወጥ ከውስጥም ከውጭም ያላችሁ ኢትዮጵያውያን አንድ አድርጎ ለማድመቅና የችግሯን ሰንኮፍ መንግሎ ለመጣል ሰላምና ዲሞክራሲ ዕድገትና ብልጽግናን ለማጎናጸፍ፣ አገር ለማቅናት ጥሩ ምክንያት ያላችሁ ሰዎች ለአገር ዘብ መቆም ይገባችኋል።

# “ያገሩን ሰርዶ ባገሩ በሬ“ በቀላሉ የሚታይ አይደለም

ግርማ መንግሥቴ

ሁሌም ሲባል እንደሚሰማው፣ እንደሚነገረውና እኛም እንደምናውቀው ግብረ ሰናይ ድርጅቶች፣ በጎ አድራጎት ተቋማትና ማህበራት የምን ጊዜም የልማት አጋሮች ናቸው። ንቁና ተሳትፎ አሳታፊ ሲቪክ ማህበረሰብ ከመፍጠር አኳያም የሚጫወቱት ሚና ቀላል አይደለም። ይህ ማለት በጤናማው አመለካከትና ተገቢ በሆነው በእነሱ ሰብአዊ ተግባር ላይ የተመሰረተ ድምዳሜ ሲሆን፤ ከአላማው ውጪ ውሎ ከተገኘ ግን ምላሹ ተቃራኒ ነው፡ ፡ ምድቡና ትርጓሜውም ሌላ ይሆናል፡፡

የበጎ አድራጎት ተቋማትን ታሪክ በሀገራችን የሚነሳው ከ1965 ዓ.ም ነው፡፡ በወሎና ትግራይ ከፍተኛ ድርቅ በመከሰቱ ምክንያት ቁጥራቸዉ በርከት ያሉ መንግሰታዊ ያልሆኑ ዕምነት ተኮር ድርጅቶች ተፈጥረዋል፡፡ በዚህም ቀላል የማይባል ሰብአዊ ድጋፍና ተሳትፎ መደረጉን በድርሳናት ሰፍሮ እናገኘዋለን። ይህ ደግሞ በሺህ ለሚቆጠሩ፣ ለዛሬዎቹ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች መፈጠር ምክንያት ሆኗል። ከአስር ዓመት በኋላም እንዲሁ እንደገና በ1977 ዓ.ም ድርቁ በተመሳሳይ በወሎና ትግራይ አካባቢ በስፋት ሲከሰት እነዚህ ድርጅቶች ደርሰው በድጋፋቸው ችግሩን አቅለውታል፡፡ ለመቋቋምም አስችለዋል።

በአገራችን አጠቃላይ ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች መፈጠርና ወደ ተግባር መግባት ታሪካዊው መነሾ ይሄው ነው። በተለይም ከደርግ ዘመን በኋላ ወደ ስራ በገባው ሕገመንግስት የመደራጀት መብትን በመጠቀም በርካታ የሃገር ውስጥና የውጭ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መፈጠር ችለዋል። ይህን ስንል ግን የመረዳዳት ባህል፣ የመደጋገፍና በጋራ ችግርን ተጋፍጦ በጋራ መፍትሄ ማምጣት ወዘተ በአገራችን አልነበረም ማለት አይደለም፡ ፡ አለ፤ ነበርም። በመኖሩም ነው በተለይ በአሁኑ ወቅት ”አገር በቀል እውቀት”ም ሆነ የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ”አገር በቀል ኢኮኖሚ” የሚሉት ጽንሰ-ሀሳቦች እንደ ገና ልዩ ትኩረትን አግኝተው የሁሉም መነጋገሪያና ርእሰ ጉዳይ ሊሆኑ የበቁት። ችግሩ ተግባራዊነቱ ካልሆነ በስተቀር ማለት ነው።


ሁሌም ”በኢትዮጵያ አገር በቀል እውቀቶች ተጠብቀውና ዳብረው ለትውልዱ እየተላለፉ ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ ረገድ ምሁራን በሚፈለገው ደረጃ ሚናቸውን እየተወጡ እንዳልሆነ» ጥናቶች የሚያመላክቱ ሲሆን፤ በቅርቡ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ከአምቦ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር በአምቦ ዩኒቨርሲቲ አዳራሽ፣ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በተሳተፉበት አካሂዶት በነበረው ኮንፈረንስ ላይም የተረጋገጠው ይኸው ነው። መፍትሄውም ”መስራት፣ ዘርፉን ማልማት ይገባል” የሚል ነው፡፡ ይህ አገር በቀል እውቀትን ወደ ተግባር ከመቀየር አኳያ ችግር መኖሩ የተገለፀው በጥናትና ምርምር ስራዎች ብቻ አይደለም፡፡ አዲስ ዘመን ከአነጋገራቸው የተለያዩና በየደረጃው ከሚገኙ አካላትም ነው፡፡

በኦሮሚያ ክልል የቡሶ ጎኖፋ ቢሮ ምክትል ሀላፊ አቶ ገረመው ኦሊቃ ከአዲስ ዘመን ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንደ ገለፁት፤ እኛ አገር በቀል እውቀትን ተጠቅመናል፤ ወደ ተግባር ቀይረነዋል ማለት አንችልም። እንደ አገር ካየነውም ምንም የተሰራ ስራ የለም። በመሆኑም በዚህ ዘርፍ ጠንክረን ልንሰራ ይገባል። ሁሉም በየክልሉ ያለውን አገር በቀል እውቀት ለይቶ በማውጣትና በማልማት ወደ አገራዊ ተጠቃሚነት ማምጣት አለበት።

አክለውም፣ በኦሮሚያ ክልል በጉዳዩ ላይ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ የሚገኝ ሲሆን፤ አንዱም የገዳ ስርአት አካል የሆነውን ”ቡሶ ጎኖፋ”ን ወደ ዘመናዊ ተቋምነት የመቀየሩ ስራ ነው፡፡ እሱም ተከናውኗል። (ባለፈው ሳምንት በዚሁ አምድና ገጽ ላይ የወጣውን ጽሑፍ ይመልከቱ።)

### ያለንበት ሁኔታ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ”የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የፕሮጀክት አፈጻጸምና ክትትልን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት” (ጥር 2006 ዓ.ም)፤ ”በኢትዮጵያ ዘመናዊ የመንግስት አስተዳደር ሕግና ስርዓትን በተከተለ መልኩ በጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራትን መመዝገብ፣ ማስተዳደርና መቆጣጠር የተጀመረው በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ሲሆን፣ በወቅቱ የአገር ግዛት ሚኒስቴር ተብሎ ይጠራ



የነበረው መንግስታዊ ተቋም በ1952 ዓ.ም በወጣው የፍትሐብሔር ሕግ ከቁጥር 404እስከ 549 ባሉት ድንጋጌዎችና በዝርዝር ለማስፈፀም በ1952 ዓ.ም በወጣው የማህበራት ምዝገባ ደንብ ቁጥር 321/1959 መሠረት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን ሲመዘግብ ቆይቷል፡፡” በማለት ከገለፀ በኋላ፤ ከወታደራዊው መንግስት (ደርግ) በኋላ ባለቤት አጥቶ እዚያና እዚያ ሲል መቆየቱን፤ በተለያዩ ጊዜያትም በተለያዩ ተቋሟት ሲተዳደር መኖሪን ይናገራል። ከዛስ?

በዚሁ አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 621/2001) አንቀጽ 8 መሠረት በመንግስት በተሰየሙ ሰባት አባላት በሚመራ ቦርድ የሚተዳደር የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ኤጀንሲ እንደ አንድ የፌደራል የመንግስት መስሪያ ቤት ለፍትህ ሚኒስቴር ተጠሪ ሆኖ በመቋቋም ከመስከረም 2002 ዓ.ም ጀምሮ በአዋጁ የተቀመጡትን ተልዕኮዎች ለመፈጸም እየሰራ ይገኛል፡፡ የፌደራል አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 የኤጀንሲው ተጠሪነት ለፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር እንዲሆን ተደረገ፡፡ ከዚህ በኋላስ?

በፈረንጆቹ በ2019 የተገኘ መረጃ እንደሚያመለክተው በሃገራችን ከ3ሺህ፤ በክልል ደግሞ ከ1ሺህ የሚልቁ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አሉ። የበጎ አድራጎት ድርጅቶቹ ባላቸው አደረጃጀትና የሚሰማሩባቸውን አላማዎች መሠረት በማድረግ፤ ተመሣሣይና ተቀራራቢ አላማ ያላቸውን በመለየት፣ በአዋጅ 621 /2001 መሠረት የተቋቋመው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ”የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን የዓላማ ማስፈፀሚያና አስተዳደራዊ ወጪዎችን መወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 2/2003” በሚል ርእስ ባረቀቀውና ”ይህ መመሪያ ከጥር 15 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡” በሚለው ሰነድ መሰረት በኢትዮጵያ ውስጥ በሚከተሉት አስር ዘርፎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እንዲንቀሳቀሱ ተደረገ፡፡ ዘርፎቹም፡-

በሴቶችና ህፃናት ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች፤ በኤች.አይቪ.ኤድስ መከላከል እና ጤና ማስፋፋት ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች፤ በግብርና፣ ምግብ ዋስትና፣ ሕይወት ማዳንና አካባቢ ጥበቃ ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ፤ በትምህርት ማስፋፋት ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ፤ በአካል ጉዳተኞች፣ ጎዳና ተዳዳሪዎችና አረጋዊያን በመደገፍ ስራ የሚንቀሳቀሱ፤ በባህል፣ ቅርስ፣ ወጣቶችና ስፖርት ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ፤ በሰብዓዊና ዴሞክራሲያው መብቶች ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ፤ በግጭት አፈታት፣ የፍትህና የሕግ አፈጻጸም ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ፤ በአቅም ግንባታ፤ ምርምርና ጥናት ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ፤ በስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ናቸው።

ኤጀንሲው ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በአገሪቱ 3ሺህ 115 የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ተመዝግበው በሥራ ላይ ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ 416 የውጭ አገር በጎ አድራጎት ድርጀቶች፣ 2ሺህ 646 በኢትዮጵያ ውስጥ የተደራጁ (አገር በቀል) በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት፤ እንዲሁም 53 ኅብረቶች ናቸው በማለት ያስነበበን ሪፖርተር ጋዜጣ (17 ኦገስት 2016) ነው፡፡

በሃገራችን ያሉ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ጤና፤ የህጻናት ልማት፤ ትምህርት፤ ማህበራዊ ድጋፍ፡ አቅም ግንባታ፤ ገቢ ማስገኛ አካባቢ ጥበቃ እና እርሻ ስራና የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡ ከዚሁ ከበጎ አድራጎት ወይም መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች (ኤንጂኦ) ጋር በተያያዘ ብዙ ጊዜ የሚሰማው ነገር ድርጅቶቹና ማህበራቱ ለህብረተሰቡ ከሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ይልቅ የግለሰቦች የሀብት ምንጭና መጠቀሚያ ተደርገዉ የመታየታቸው ጉዳይ ሲሆን፤ ይህ ጽሑፍ በአሁኑ ሰዓት የዚህ አይነቱ አተያይ እየከሰመ፣ በጎ አድራጎት ድርጅቶቹም ወደ ሰብአዊ ተግባራቸው በማተኮር ህብረተሰብን በማገልገል ላይ ናቸው በሚል ታሳቢ የቀረበ ነው።

በአንድ ወቅት ሲነገርለት የነበረው (አሁን አለ?) ”የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መድረክ” የድርሻውን ይወጣል የሚለውም እንደ ታሳቢ ተወስዷል። ”መንግስት ለምን የመቆጣጠሪያ አሰራርን ዘረጋ?” የሚለው ቅሬታም ተወግዷል ተብሉ ይታሰባል። ያም ሆኖ ግን ኤጀንሲው ወደ ስራ እንደ ገባ ባደረገው ምርመራና የማጣራት ስራ መሰረት፤

”የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ከታዩባቸው ችግሮች መካከል ከተቋቋሙለት ዓላማ ውጪ መንቀሳቀስ፣ ያለኤጀንሲው ፈቃድ የባንክ አካውንት መክፈት፣ የገቢ ምንጫቸውን አለማሳወቅ፣ ዓመታዊ የሥራና የኦዲት ሪፖርት በወቅቱ አለማቅረብ፣ የቋሚ ንብረት ዝርዝር አለማሳወቅ፣ የፕሮጀክት ስምምነት ሳይፈራረሙ መሥራት፣ አስተዳደራዊ ወጪዎችን ከዓላማ ማስፈጸሚያ ወጪዎች ጋር መቀላቀል፣ አስተዳደራዊ ወጪ ከ30 በመቶ በላይ መጠቀም፣ ልማትን ከሃይማኖት ጋር ቀላቅሎ መሥራት፣ ያለፈቃድ የገቢ ማስገኛ ሥራዎች ላይ መሰማራት ለአብነት የሚጠቀሱ ግኝቶች ናቸው፡፡ [... በመሆኑም] በ2008 በጀት ዓመት 122 የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ተዘግተዋል፡፡

[...] ባክነር አዶፕሽን ኤንድ ማተርኒቲ ሰርቪስ፣ ግሎባል ኢንፋንቲልና ሜዲስን ዱሞንድ የተባሉ ሦስት የውጭ በጎ አድራጎት ድርጅቶች በፈጸሙት የሕግ ጥሰት ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸውም ያሉባቸውን ችግሮች ባለማስተካከላቸው ተዘግተዋል፡፡ [...] መሥፈርቱን ያሟሉ 187 የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ተመዝግበዋል፡፡ ለ803 የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የፈቃድ እድሳት ተሰጥቷል፡፡” በማለት ያሰፈረውን ሪፖርት መጥቀሱ ተገቢ ይሆናል።

### ወደ አገር በቀሉቹ እንምጣ

”ሰውን ለመርዳት ሰው መሆን ብቻ በቂ ነው።” በሚል መርህ የሚመራው ሜቄዶኒያ የአረጋውያንና የአዕምሮ ህሙማን መርጃ ማዕከል ዛሬ የደረሰበትን ደረጃና እየሰጠ ያለውን ማህበራዊ አገልግሎት በተመለከተ በማእከሉ ማደግና መስፋፋት መገረም ብቻ ሳይሆን፤ በ”ይቻላል!!!” ሁሉ እንደሚደመም ምንም ጥርጥር የለውም።

በታህሳስ 2002 ዓ.ም የቤተሰቦቻቸውን ቤት መነሻ አድርገው በ10 ተረጂዎች የተጀመረው ይህ ማእከል በመስራቹና ተግባሩን ”የሕይወቴ ጥሪ ነው” ሲሉ በሚገልፁት አቶ ቢኒያም በለጠ የሚመራ ሲሆን፤ ከተቋቋመበት አላማ ሌላ ሌሎች በርካታ መሰል ድርጅቶች እንዲፈጠሩ አርአያ ለመሆን የበቃ የአሁኑ ትልቅ፣ የወደ ፊቱ ግዙፍ ተቋም ነው።

ተቋሙ አረጋውያንና የአዕምሮ ሕሙማንን ከጎዳና በመሰብሰብ የላቀ ሰብዓዊነት ያለው፤ ከላይ በጠቀስነው መርህ የሚመራ ዓመታትን ያስቆጠረም ነው። አሁንም አካል ጉዳተኞች፣ አረጋዊያንና ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ ለማመቻቸት በክልሎች እየተዘዋወረ፤ የግንባታ ስፍራዎችን እየተረከበና እየገነባም ይገኛል። በባህር ዳር፣ ድሬ ዳዋ፣ ኢሉ አባቦራ፣ ጎሬ ... ቦታዎችን ተረክቧል፤ ወደ ግንባታ የተሸጋገረባቸው አካባቢዎችም አሉ።

እኤአ ኤፕሪል 11፣ 2021 ይፋ በሆነ ዜና እንደ ተነገረው፤ ማዕከሉ በአዲስ አበባና በክልል ከተሞች የተረጂዎችን ቁጥር በሦስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ወደ 10ሺህ ለማድረስ እየሰራም ይገኛል። አረጋውያንንና አዕምሮ ህሙማንን መሰረታዊ ፍላጎት ከማሟላት ባሻገር አምራች ዜጋ በማድረግና እና ከተረጂነት ተላቀው እንዲኖሩ በማስቻል ረገድ በርካታ ስራዎችን በመስራት ላይ ነው። ለዚህ ሁሉ ስኬቱ፣ የህዝቡን ድጋፍ ለማግኘቱ፣ የህብረተሰቡ ተሳትፎና የእርዳታ ፈላጊዎቹ ተጠቃሚነት ዋናውን ድርሻ የተጫወተው የማእከሉ አገር በቀልነት መሆኑ በብዙ መልኩ ተረጓግጧልና ሌሎች ይማሩበታል ተብሎም ይታሰባል።

ተስፋ አይነ ስውራንና አካል ጉዳተኞች ማቋቋሚያ ማዕከል፣ ፍቅር ለሕፃናትና ለእናቶች የበጎ አድራጎት ድርጅት፣ ሙዳይ፣ ኢንስፓየርድ ኢትዮጵያ ዩዝ አሶሲየሽን፣ ሀገር ፍቅር በጎ አድራጎት ማህበር፣ የኮቪድ-19 መከሰትን ተከትሎ የተፈጠሩ በርካታ ማህበራትና ድርጅቶች (ለምሳሌ ዱብቲ በጎ አድራጎት ማህበር) ወዘተ እያለ የሚቀጥል የበርካታ መንግስታዊ ያልሆኑ፤ አገር በቀል እርዳታ ድርጅቶችና ማህበራት ተቋቁመው ሰብአዊ ድጋፎችን በማድረግና ሀላፊነታቸውን በመወጣት ላይ ይገኛሉ።

ይህ በየትኛውም መልኩ የሚበረታታ ሲሆን፤ ችግሩና አሳሳቢው ጉዳይ የት ይደርሳሉ የሚባሉት እነዚህ ማህበራዊና ሰብአዊ ተቋማት ብቅ ጥልቅ የማለታቸው፣ እየታዩም የመክሰማቸው ጉዳይ ነው። ለዚህም ነው ብዙዎቹ ከእነ ሜቄዶኒያ ትምህርትንና ልምድን ሊወስዱ ይገባል የምንለው። ወደ ማሳያችን እንዝለቅ፤

”መሠረት በጎ አድራጎት ድርጅት” ይባላል። የተመሰረተው ቅን ልቦና ካላቸው ዜጎች አንዷ በሆኑት ወይዘሮ መሰረት አዛገ ነው። ታዳጊ እናቶች እና ልጆቻቸውን ከጎዳና ላይ አንስቶ ከመርዳት ባለፈ ልዩ ልዩ ስልጠናዎችን በመስጠት እራሳቸውን እንዲችሉ በማድረግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡ ይህ አገር በቀል በጎ አድራጎት ድርጅት፤ በአንድ ወቅት ”መሰረት የበጎ አድራጎት ድርጅት 15ሺህ ለችግር የተጋለጡ ህፃናትና ሴት ተማሪዎችን ለትምህርት ለማብቃት የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም አደረገ” የሚል ተስፋ ሰናቂ ዜና ሲነገርለት እንደነበረ የሚታወስ ነው።

በለጋ እድሜ የልጅ እናት መሆን የሚያመጣውን ችግር ለመቅረፍ በጎዳና ላይ የወደቁ እናቶችን በመሰብሰብ እና መጠለያ በመስጠት የተሃድሶ መርሃግብር እንዲያገኙና በኋላም ቤት ተከራይተው እራሳቸውን ችለው እንዲወጡ ለመርዳት እራሷ እየመራች የምትገኘው መሰረት፤ በአሁኑ ሰዓትም አንዳንድ የሚደርሱባትን ጫናዎች ቢኖሩም ችግሩን ተቋቁማ ተግባሯን አስቀጥላለች፡፡ በዚህም ከበርካቶች ”እናታችን” የሚል መጠሪያን አትርፋበታለች።

ከአዲስ ዘመን ጋር ቆይታ ካደረጉት፣ በ”መሰረት የበጎ አድራጎት ድርጅት” እየታገዙ ከሚገኙትና ልዩ እንክብካቤን እያገኙ ካሉት መካከል አንዷ የሆነችውና የልጅ እናቷ እመቤት ከበደ እንደነገረችን፤ ሁሉ ነገር ልዩ ነው። እናትና አባት የማያደርገው ሁሉ ይደረግላታል፡ ፡ በአሁኑ ሰዓትም መንጃ ፍቃድ ለመያዝ እየሰለጠነች ሲሆን፤ ስትጨርስም ባጃጅ ለመያዝና እራሷን ለመቻል እቅድ አላት፡፡

ሌላዋ፣ የልጅ እናትዋና የልብስ ስፌት ማሽን ስልጠና እየወሰደች ያለችው ሀረግ አለሙ ትባላለች፡፡ ከድርጅቱ ተጠቃሚ እንደሆነችና ድርጅቱ ከቤተሰብም በላይ እየተንከባከባቸው እንደሚገኝ ነግራናለች። በአጠቃላይ በየትም አገር በጎአድራጎት ድርጅቶች ያስፈልጋሉ። በመሆኑም በብዛት ሊኖሩ፣ ከሚመለከታቸው አካላትም አስፈላጊው ሁሉ ሊመቻችላቸው፤ እነሱም የሚጠበቅባቸውን በአግባቡ ሊያደርጉ .... ይገባል። ይህንን ሁሉ ስንልም፣ ለአንድ አገር ሁለንተነዊ እድገት የአገር በቀል ተቋማት ሚና የሚተካ አለመሆኑን፤ በብዛትም ሊፈጠሩ የሚገባ መሆኑን ከስሩ በማስመር ነው።

# ተመራቂ ወጣቶች ላይ ያተኮረ የሥራ ዕድል ፈጠራ

**አስናቀ ፀጋዬ**

ኢትዮጵያ በርካታ ቁጥር ያለው ወጣት እንዳላት በተደጋጋሚ ይነገራል። ለዚህ በርካታ ቁጥር ያለው ወጣት ግን አጥጋቢ በሆነ መልኩ የሥራ እድል ሲፈጠር አይታይም። ለወጣቱ ኅብረተሰብ የሥራ እድል ለመፍጠር በመንግሥት በኩል የሚደረገውም ጥረት አርኪ አይደለም። የግሉ ዘርፍ ለበርካታ ወጣቶች የሥራ እድል ይፈጥራል ተብሎ ቢታሰብም በልዩ ልዩ ምክንያቶች የሚጠበቅበትን ድርሻ አልተወጣም።

በኮቪድና በተለያዩ ሁኔታዎች የዓለም ኢኮኖሚ መንገራገጭ ብሎም የኢትዮጵያ የፀጥታ ችግርም ለወጣቶች በሚፈለገው ልክ የሥራ እድል ለመፍጠር አላስቻለም። በዚህና በሌሎች ምክንያቶች ከተለያዩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተመርቀው የሚወጡ ተማሪዎችም ያለሥራ ለመቀመጥ ተገደዋል። በዛው መጠን በብዙ ወጣቶች ዘንድ ተቀጥሮ ከመሥራት ይልቅ የራስን ሥራ የመፍጠር ፍላጎት ደካማ መሆንም ችግሩን ይበልጥ አባብሶታል።

በነዚህ ችግሮች ውስጥ ታዲያ አሁንም ተስፋ ሰጪና የወጣቱን ሕይወት የሚቀይሩ የሥራ እድል ፈጠራዎች በፌደራልና በክልል ደረጃ እየተከናወኑ ይገኛሉ። በተለይ ደግሞ በሲዳማ ክልል ወጣት ተመራቂ ተማሪዎች ላይ ትኩረት አድርጎ እየተከናወነ ያለው የሥራ እድል ፈጠራ ለዚህ አይነተኛ ማሳያ ነው።

አቶ ከፍያለው ከበደ የሲዳማ ክልል ሥራ፣ ክህሎትና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ ምክትል ኃላፊና የገጠር ሥራ እድል ፈጠራ ዘርፍ ኃላፊ ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት ክልሉ በገጠር ሥራ እድል ፈጠራ በዘጠኝ ወራት ውስጥ የተሻለ አፈፃፀም አሳይቷል። በዝግጅት ምዕራፍም ክልሉ በማይንድ ሴትና ኢንተርፕሪነርሽፕ ስልጠናዎች ላይ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን አከናውኖ ወደተግባር ገብቷል።


ይህንኑ መነሻ በማድረግም ክልሉ በተለይ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የተመረቁ ወጣቶች ላይ ትኩረቱን በማድረግ የሥራ እድል ፈጥሯል። በዚህም እስከ ዘጠነኛ ወር ድረስ 26 ሺ 373 ለሚሆኑ ወጣቶች በግብርና፣ በኢንዱስትሪና አገልግሎት ዘርፎች ቋሚ የሥራ እድል ተፈጥሯል። ይህ ሲባል ግን በጊዜያዊነት ለወጣቶች የሥራ እድል አልተፈጠረም ማለት አይደለም። በጊዜያዊነት የሥራ እድል የተፈጠረላቸውን ወጣቶች በመደገፍና በማብቃት ቆጥበው ወደቋሚ ሥራ እንዲመጡ ጠንካራ ሥራዎች ተሠርተዋል።

ይህ አፈፃፀም በዓመቱ ከታቀደው ጋር ሲነፃፀር 78 ከመቶ መሆኑን ያሳያል። ከዘጠኝ ወሩ እቅድ አፈፃፀም ጋር ሲታይ ደግሞ 89 ከመቶ ያህሉን ማሳካት ተችሏል። የሥራ እድል የሚፈጠርላቸው ወጣቶችን ልየታ በሚመለከትም መቶ በመቶ ማሳካት ተችሏል። ልይታን በተለመደው መንገድ ብቻ ሳይሆን የዳታ ቤዝ ሥርዓት በመፍጠር ከታች የሚመጡ መረጃዎች በኮምፒዩተር ሥርዓት ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ በመቻሉ ልየታውን በሚፈለገው ልክ ማሳካት ተችሏል። በዚህም ቀደም ሲል የነበረው የመረጃ ጥራትና ድግግሞሽ ችግር ተወግዷል።

ከዚህ ባለፈ ለወጣቶቹ የመሸጫና የማምረቻ ቦታዎች ድጋፎች ተደርገዋል። የብድር አቅርቦትና የብድር አገልግሎቶችም ተሰጥተዋል። የሂሳብ ዝርጋታና የኦዲት ሥራዎችም ተሠርተው ኢንተርፕራይዞችን ወደፊት የማሸጋገር ሥራዎችም ተከናውነዋል።

ምንም እንኳን ክልሉ የመሬት ጥበት ችግር ያለበት ቢሆንም በመንግሥታዊ ድጋፍ መሬቶቹ ለሥራ እድል ፈጠራ እንዲውሉ በማድረግ በአግባቡ ተጠቅሟል። በተለይ ደግሞ በክልሉ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች አካባቢ የሚገኙ ሰፋፊ መሬቶችን ለወጣቶች የሥራ እድል ፈጠራ እንዲውሉ በማድረግ ለተሞክሮ የሚሆን ሥራዎችን አከናውኗል።

ለአብነትም በሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ በአጭር ግዜ 85 ሄክታር የሚሆን የትምህርት ቅጥር ግቢ ውስጥ ያሉ መሬቶችን በዲግሪ ለተመረቁና ለ75 ወጣቶች በማቅረብ የትራክተር ድጋፍ ተደርጎላቸው በግብርና ዘርፍ ተሰማርተው ተጠቃሚ መሆን ችለዋል። ሌሎች የወል መሬት ያሉበትንም በውል ለሶስትና ለአራት ዓመታት ወጣቶቹ እንዲጠቀሙበት ተደርጓል።



ፎቶ ፎቶ፡-በሃዱሽ አብርሃ

አቶ ከፍያለው ከበደ፤

> **በበጀት ዓመቱ 38 ሺ 605 ለሚሆኑ ወጣቶች የሥራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ እስከ ዘጠነኛ ወር ድረስ 26 ሺ 373 ያህሉን ማሳካት ተችሏል። ቀሪውን ደግሞ ለማሳካት ለሶስት ወራት በማከፋፈል ተቀምጧል**

እንደ ኃላፊው ገለፃ በመንግሥት ድጋፍ እንደ ክልል 60 ሚሊዮን ብር በመያዝና ሁሉም ገንዘብ ወደታች እንዲወርድ በማድረግ ለሥራ እድል ፈጠራ እንዲውል ተደርጓል። ከዚህ ቀደም የተሰራጩ ብድሮችም በብድር አስመላሽ ግብረ ኃይል እንዲመለሱ በማድረግ ለወጣቶች የሥራ እድል ፈጠራ እንዲውል እየተደረገ ይገኛል።

በዚህም እስከ ዘጠነኛ ወር ድረስ መመለስ ከሚገባው 100 ሚሊዮን ብር ውስጥ 44 ሚሊዮን ብር ያህሉን ማስመለስ ተችሏል። ይህ አምና ከነበረው አፈፃፀም ጋር ሲታይ ደግሞ የተሻለ ለውጥ አሳይቷል። በሌላ በኩል ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ለተመረቁ ወጣቶች ቅድሚያ በመስጠት እስከ ዘጠነኛው ወር ድርስ 46 ሚሊዮን ብር ብድር ተሰራጭቷል። ነገር ግን አምና እስከዘጠነኛ ወር ድረስ የተሰራጨው የብድር መጠን 22 ሚሊዮን ብር በመሆኑ የዘንድሮው አፈፃፀም ከአምናው በእጥፍ የተሻለ ነው።

ክልሉ በዚህ ዓመት 3 ሺ 500 ኢንተርፕራይዞችን ወደቀጣዩ ደረጃ ለማሸጋገር አቅዶ እስከ ዘጠነኛ ወር ድረስ 483 ያህል ኢንተርፕራይዞችን ብቻ ማሸጋገር ችሏል። ይህም ከተያዘው እቅድ አኳያ ሲታይ አፈፃፀሙ ጉድለት እንደሚታይበትና ለዚህ ጉድለት ምክንያቱ የባለሙያ ድጋፍ እጥረትና ወቅታዊ ሀገራዊ ሁኔታ መሆኑን አረጋግጧል። ይህንኑ ችግር ለመቅረፍም ባለሙያዎች እንዲቀጠሩ ተደርጓል። የባለሙያዎቹን ክህሎት ለማዳበርም ስልጠናዎች ተሰጥቷቸዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ የሚደራጁ ኢንተርፕራይዞች በቶሎ እንዳይበተኑና ዘላቂነት እንዲኖራቸው በጥራት ረገድ ጠንካራ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ። ለዚህም አንዳንድ ሪፎርሞች እየተከናወኑ የሚገኝ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ አንዱ እንደ ክልል የተዘጋጀው የብድር ጣሪያ ወይም የፓኬጅ ጥናት ሪፎርም ነው። በዚህ ሪፎርም ቀደም ሲል የነበሩትን ሀያ ሦስት ፓኬጆች አዳዲሶችን በማካተት ወደ አርባ ስድስት እንዲያድጉ ተደርጎ ወደ ሁሉም ወረዳዎች ወርዷል።

ይህ ሪፎርም ሊደረግ የቻለውም አሁን ባለው ሁኔታ የኑሮ ውድነቱ ጋር በተያያዘ አንዳንድ ቀደም ሲል የነበረው የገንዘብ ዋጋ አሁን ካለው ጋር የሚመጣጠን ባለመሆኑ ነው። ለአብነትም በዶሮ እርባታ የአንድ ቀን ጫጩት 15 ብር እያለ ነበር ፓኬጁ የተጠናው። ይሁንና በአሁኑ ወቅት የአንድ ቀን ጫጩት ዋጋ በመጨመሩ ዋጋው እንዲስተካከል ተደርጓል። በተመሳሳይ በሌሎች ፓኬጆች ላይም የዋጋ ማሻሻያ ተደርጓል።

በሌላ በኩል ደግሞ ከዚህ ቀደም ተፈጥሯዊ ማዳበሪያ የማምረት ሥራ በፓኬጅ ውስጥ ያልነበረ በመሆኑ እንዲገባ ተደርጓል። በክልሉ ሦስት ወረዳዎች የሚሠራው የሐር ትል ማምረት ሥራ እንደ አንድ ፓኬጅ ተቆጥሮ ተካቷል። ፓኬጆቹን ክላስተር የማድረግ ሥራም ተከናውኗል። በዚሁ መሠረት የፍየልና በግ ማሞከቻ፣ የወተት ላም፣ የዶሮና የሰብል ክላስተሮች በሚል የመለየት ሥራም ተሠርቷል። ፓኬጆቹን በክላስተር የመለየት ሥራ የተከናወነውም በዋናነት ውጤታማነቱን ይበልጥ ለመጨመር ነው።

በክልሉ 538 የገጠር ቀበሌዎች ያሉ ሲሆን በነዚህ ቀበሌዎች ውስጥ ባለሙያዎች ተመድበዋል። ይሁንና ባለሙያዎቹና በነዚህ ገጠር ቀበሌዎች ውስጥ ያሉት ሀብቶች የሚገኙት በተበታተነ ሁኔታ ነው። ይህንኑ ታሳቢ በማድረግም በዳሌ ወረዳ በሙከራ ደረጃ ተጀምሮ ተበታትነው የነበሩ ባለሙያዎች ወደ አንድ ማዕከል እንዲመጡ ተደርጓል። በሌላ አባባል ሦስትና አራት የሚሆኑ ቀበሌዎች ዘመናዊ በሆነና ለመረጃ አያያዝ በሚያመች መልኩ ወደ አንድ ማዕከል ታቅፈዋል።

በቀጣዩ 2015 ዓ.ም ከተማ ላይ ያለው የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ በገጠር ወረዳዎች ላይም ተግባራዊ እንዲሆን ታሳቢ በማድረግ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ።

ኃላፊው እንደሚያብራሩት ከዚህ በፊት በክልሉ የሚገኙ ተመራቂ ወጣቶች በአብዛኛው ፔሮል ላይ መፈረምን ብቻ ነበር የለመዱት። ሥራቸውን እንደጨረሱ መንግሥት ሥራ ይፈጥርልኛል ብለው ነበር የሚያስቡት። ነገር ግን በአሁኑ ግዜ በተለይ በአስተሳሰብ ለውጥ ላይ ጠንካራ ሥራ በመሠራቱና ተደጋጋሚ ስልጠናዎችም በመስጠታቸው በዲግሪ የተመረቁ ቁጥራቸው በርከት ያሉ ወጣቶች ራሳቸውን ሥራ ፈጥረው ወደ ሥራ እንዲገቡ ተደርጓል።

በዚህም ወደ 2 ሺ 673 የሚሆኑ የዲግሪ ምሩቃን ወጣቶች የራሳቸውን ሥራ ፈጥረው ወደ ሥራ ገብተዋል። በተመሳሳይ ቁጥራቸው በርከት ያለ የዲፕሎማ ተማራቂ ወጣቶች የራሳቸውን ሥራ ፈጥረዋል።

በክልሉ የሚገኙ የተፈጥሮ ፀጋዎችን በመለየትም ምሩቃኖች እንዲደራጁና እነዚህ የተፈጥሮ ፀጋዎች እንዲጠቀሙባቸው ተደርጓል። በተለይ ደግሞ ወጣቶቹ በወርቅ፣ ሴራሚክና ማዕድናት ማውጣት ሥራ ላይ ተደራጅተው የሥራ እድል ተፈጥሮላቸዋል። በአንዳንድ የወርቅ ማዕድናት በሚገኙባቸው አካባቢዎች ኩባንያዎች ወደ ቁፋሮ ከገቡ በኋላ ለወጣቶቹ በንዑስ ሥራ ተቋራጭ ዘርፍ የሥራ እድል እንዲፈጠርላቸው ተደርጓል። በአሸዋና ድንጋይ ማዕድንም ወጣቶቹ ቅድሚያ አግኝተው እንዲሠሩ ተደርጓል።

በሌላ በኩል ደግሞ በየትኛውም ካፒታል ሥራና በትላልቅ ፕሮጀክቶችም የሚሠሩትም ጭምር ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ትምህርታቸውን አጠናቀው ለወጡ ወጣቶች ቅድሚያ ተሰጥቶ እንዲሠሩ ተደርጓል። ትላልቅ የግንባታ ሥራዎችም ካሉ ስልጠና ተሰጥቷቸው ወጣቶቹ የንዑስ ተቋራጭ ሥራ እንዲያገኙ ይደረጋል።

ለአብነትም በሀዋሳና አጎራባች ከተሞች ላይ በአረንጓዴ ስፍራ፣ በማፋሰሻ ቦይ፣ በኮብል ስቶንና በመንገድ ሥራዎች ትምህርታቸውን ጨርሰው የመጡ ወጣቶች እንዲገቡ ተደርጓል። በተመሳሳይ በገጠርም ተመራቂ ወጣቶቹ በገጠር ተደራሽና ቀበሌን ከቀበሌ በሚያገናኙ የመንገድ ግንባታ ሥራዎች ተደራጅተው እየሠሩባቸው ይገኛሉ።

ኃላፊው እንደሚገልፁት በክልሉ የሥራ እድል በገጠርና በከተማ የሚፈጠረው በግብርና፣ በኢንዱስትሪና በአገልግሎት ዘርፍ ሲሆን በዋናነት ግን በግብርናው ላይ ልዩ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ ይገኛል። በዚህም እስከ ዘጠነኛ ወር ድረስ ሥራ ከተፈጠረላቸው 26 ሺ 373 ወጣቶች መካከል 80 ከመቶ ያህሉ በግብርና ዘርፍ የሥራ እድል የተፈጠረላቸው ናቸው። ይህም የእንስሳት ሃብቱን፣ የወተት ላም፣ ከብት ማድለብ፣የአንድ ቀንና አርባ ስምንት ቀን ጫጩት፣ ዶሮ፣ እንቁላልና ስጋን ያካትታል።

በተለይ በእንስሳት ዘርፍ ይርጋለም ላይ ባለው የአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ አማካኝነት ወጣቶች ለፓርኩ የግብርና ምርቶችን በግብዓትነት እንዲያቀርቡና እዛው በፓርኩ ውስጥ ገብተው እንዲሠሩ በማድረግ የሥራ እድል ተፈጥሮላቸዋል።

በኢንዱስትሪ ዘርፍም በተለይ በኮንስትራክሽን ሥራ ከወርቅ ማምረት አንስቶ እስከ መንገድ ግንባታ ድረስ ያሉ ሥራዎች ላይ የተሰማሩ ወጣቶች በተመሳሳይ ሰፊ የሥራ እድል ተፈጥሮላቸዋል። በአገልግሎት ዘርፍ ደግሞ ወጣቶቹ ከፀጉር ሥራ ጀምሮ በተለያዩ የንግድ ሥራዎች ላይ ተሰማርተው ውጤታማ እየሆኑ ይገኛሉ።

ከሦስቱ ዘርፎች በዘለለ 250 የሚሆኑ ወጣቶችን ወደ ከፋ ዞን በመላክ በቡና ልማት ዘርፍ እንዲሠማሩም ተደርጓል። ወጣቶችን ወደውጪ ሀገር በመላክ ተጨማሪ ሥራዎችን ለማሠራትም ክልሉ ከክልሎችና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እየተነጋገረ ይገኛል።

በቀጣዮቹ ሶስት ወራትም ክልሉ በወጣቶች የሥራ እድል ፈጠራ ላይ ልዩ ትኩረት አድርጎ የሚሠራ ይሆናል። እስከ ዘጠኝ ወር የተሠሩ ሥራዎችን በጥንካሬና በጉድለት ከገመገመ በኋላ በሦስት ወራት ውስጥ የሚሠሩ ሥራዎችን ለየት ባለ መልኩ ገምግሞ ወደ ተግባር ገብቷል። ለዚህም ለእያንዳንዷ ቀን ስራዎችን ከፋፍሎ ሰጥቷል።

በበጀት ዓመቱ 38 ሺ 605 ለሚሆኑ ወጣቶች የሥራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ እስከ ዘጠነኛ ወር ድረስ 26 ሺ 373 ያህሉን ማሳካት ተችሏል። ቀሪውን ደግሞ ለማሳካት ለሶስት ወራት በማከፋፈል ተቀምጧል። ለሶስት ወር ከታቀደው ውስጥ ደግሞ 70 ከመቶ ያህሉን ማሳካት ተችሏል። በድጋፍና ክትትል ላይም ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ይገኛል።

# መልሶ ግንባታና ሰብአዊ ድጋፍ ላይ ያተኮረው ረቂቅ በጀት

ፍሬሕይወት አወቀ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፌዴራል መንግስቱ የ2015 በጀት አመት ረቂቅ በጀት 786 ቢሊዮን ብር እንዲሆን በቅርቡ አጽድቆ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተወያይቶ እንዲያጸድቀው ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መምራቱ ይታወሳል፡፡ የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሽዴም ባለፈው ማክሰኞ በተካሄደው ስድስተኛው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አንደኛ አመት የስራ ዘመን 11ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ ረቂቅ በጀቱን አቅርበዋል፡፡ በዛሬው የኢኮኖሚ አምዳችንም ሚኒስትሩ በቅድሚያ ኢኮኖሚውን አስመልክተው የሰጡትን ማብራሪያ ከዚያም ያቀረቡትን ረቂቅ በጀት ይዘን ቀርበናል፡፡

**ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች**

የገንዘብ ሚኒስትሩ በቅድሚያ ባለፉት አመታት በሀገሪቱ ኦኮኖሚ ላይ በአጠቃላይ የታዩ ዋና ዋና ጉዳዮችን በማንሳት ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡ አገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች ተግባራዊ በመደረጋቸው ምክንያት በአገሪቱ የተከሰተውን የተዛባ የማክሮ ኢኮኖሚ በማስተካከል ተስፋ ሰጪ የኢኮኖሚ ውጤቶች መታየታቸውንም አስታውቀዋል፡፡ ለዚህም በርካታ የገንዘብና የፊስካል ፖሊሲ፣ የውጭ ምንዛሪ፣ የፋይናንስ፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች እንዲሁም የመዋቅራዊና የዘርፍ ማሻሻያዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን ጠቅሰው፣ ይህን ተከትሎም በትክክልም የማክሮ ኢኮኖሚው የመሻሻል አዝማሚያ ማሳየት እንደቻለና በኢኮኖሚው ላይም ለውጦች እንደነበሩ ጠቁመዋል፡፡

**ፈተናዎች**

ከ2012 ዓ.ም አጋማሽ ጀምሮ የአገሪቱ ኢኮኖሚ ዘርፈ ብዙ ፈተናዎች እንዳጋጠሙትም ሚኒስትሩ ጠቅሰዋል፡፡ እነዚህም በማሻሻያዎቹ ትግበራ ውጤት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድረዋል ነው ያሉት ሚኒስትሩ፡፡

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ የኮቪድ 19 ወረርሽኝን ጨምሮ በርካታ ተግዳሮቶች አጋጥመዋል፡፡ በአንዳንድ የአገሪቱ አካባቢዎች የተከሰተው ድርቅ፣ የአንበጣ መንጋ፣ የጎርፍ አደጋና በሰሜኑ የአገሪቷ ክፍል የተከሰተው ጦርነትና ተያያዥ አለመረጋጋቶችን እንዲሁም በሩሲያና በዩክሬን መካካል የተቀሰቀሰው ጦርነትም እንዲሁ በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ካሳረፉት ዋና ዋና ችግሮች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እነዚህ ችግሮችም በቀጣይም ጫናዎችን እያስከተሉ ናቸው፡፡

ከ2011 እስከ 2013 ዓ.ም የኢትዮጵያ ምጣኔ ሀብት ዕደገት በአማካኝ በሰባት ነጥብ አንድ በመቶ ማደግ መቻሉንም የገንዘብ ሚኒስትሩ አስታውሰው፣ አፈጻጸሙ ግን ከዕቅድ በታች መሆኑን መረጃዎች አመላክተዋል ብለዋል፡፡

ሚኒስትሩ የጠቅላላ ኢንቨስትመንት አፈጻጸምን በተመለከተ በ2011 በጀት ዓመት ከነበረው የ35 ነጥብ ሶስት በመቶ ድርሻ እየቀነሰ በመምጣት በ2013 ዓ.ም ወደ 28 በመቶ ዝቅ ማለቱን ጠቅሰው፣ የዜጎች የነፍስ ወከፍ ገቢም በ2013 በጀት ዓመት ወደ አንድ ሺ 92 የአሜሪካ ዶላር ከፍ ማለቱን መረጃዎች እንደሚያመለክቱ ተናግረዋል፡፡

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ባለፉት ሁለት ዓመታት የበርካታ ዓለም አገራት ኢኮኖሚያዊ ዕድገት በከፍተኛ መጠን ቀንሰዋል፤ ከዜሮ በታች ዕድገት ያስመዘገቡ ሀገሮችም ነበሩ፡፡ ከዚህ አንጻር በአገሪቱ ተግባራዊ የተደረጉ መጠነ ሰፊ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች የተከሰቱትን ተጽዕኖዎችና ተግዳሮቶች ለመቋቋም የሚያስችል አቅም መፍጠር ማስቻላቸውን ከአፈጻጸሙ መረዳት ይቻላል፡፡

ዋጋ ንረትን በተመለከተም ባለፉት ዓመታትና በተያዘው በጀት ዓመት የዋጋ ንረት ባለሁለት አሃዝ ዕድገት በማሳየቱ የኢኮኖሚ ፈተና ሆኖ ቀጥሏል፡፡ በኢኮኖሚው ማሻሻያው አመርቂ ውጤት የልታየበት የዋጋ ንረት በታህሳስ ወር 2011 ዓ.ም ከተመዘገበው 10 ነጥብ አራት በመቶ ጀምሮ በተከታታይ ጭማሪ በማሳየት እየተጠናቀቀ ባለው 2014 በጀት ዓመት ሚያዝያ ወር ላይ የ36 ነጥብ ስድስት በመቶ የዋጋ ንረት ተመዝግቧል፡፡ የዋጋ ንረቱ የመነጨው ከምግበና ምግብ ነክ ባልሆኑ ምርቶች ላይ ሲሆን ከአቅርቦትና ፍላጎት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ለዋጋ ንረቱ መንስኤ መሆናቸውን የተካሄዱ ጥናቶች አመላክተዋል፡፡

እየተገባደደ ላለው የ2014 በጀት ዓመት ባለፈው አመት የፌዴራል መንግሥት ተጨማሪ በጀትን ጨምሮ የ675 ቢሊዮን ብር የወጪ በጀት ማጽደቁን ያስታወሱት ሚኒስትሩ፤ ይህን ወጪ ለመሸፈንም ብር 436 ቢሊዮን ከታክስ፣ ታክስ ካልሆኑና ከውጭ እርዳታ ታቅዶ እንደነበረ ተናግረዋል፡፡ የታቀደውን የበጀት ጉድለት ብር 38 ቢሊዮን ከውጭና 190 ቢሊዮን ብር ከአገር ውስጥ የተጣራ ብድር በመውሰድ ለመሸፈን ታቅዶ እንደነበርም አስታውሰው፣ በተከሰተው ጦርነት ምክንያት ተጨማሪ የወጪ ፍላጎት ከመታየቱም በላይ ከታቀደው አጠቃላይ የፌዴራል ገቢ ውስጥ እስከ 25 በመቶ የሚሆነው የታክስ ገቢና የውጭ እርዳታ የማይሰበሰብ መሆኑን ማወቅ ተችሏል ብለዋል፡፡

የጦርነቱ ጉዳትም በተያዘው በጀት ዓመት ብቻ ሳይሆን በቀጣዮቹ ዓመታትም ከፍተኛ የፊስካል ጫና እና ስጋትን የሚያስከትል መሆኑን የገንዘብ ሚኒስትሩ ጠቅሰው፣ የቀጣዮቹ ዓመታት የመንግሥት በጀት ዝግጅት ዋናው ትኩረት ከዚህ ቀደሙ በተለየ በጦርነት የደረሰውን ጉዳት መልሶ መገንባትና የሰብአዊ ድጋፍ እንዲሁም የዕዳ ክፍያ ላይ ትኩረት የሚያደርግ መሆን አመልክተዋል፡፡

> በረቂቅ በጀቱ ላይ ከተመለከተው ጠቅላላ የወጪ በጀት ውስጥ ለመደበኛ ወጪ ብር 345 ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር ለካፒታል ብር 218 ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር እንዲሁም ለክልል መንግስታት ድጋፍ ብር 213 ቢሊዮን እና ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ብር 14 ቢሊዮን ተደግፎ ቀርቧል፡፡
>
> ....
>
> የቀጣዮቹ ዓመታት የመንግሥት በጀት ዝግጅት ዋናው ትኩረት ከዚህ ቀደሙ በተለየ በጦርነት የደረሰውን ጉዳት መልሶ መገንባትና የሰብአዊ ድጋፍ እንዲሁም የዕዳ ክፍያ ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነው፡፡

**የ2015 ረቂቅ በጀት**

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተወያይቶ እንዲያጸድቀው በሚኒስትሮች ምክር ቤት ጸድቆ የተመራለት የ2015 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት ረቂቅ በጀት 786 ቢሊዮን ብር ነው፡፡ ረቂቅ በጀቱ ካለፈው በጀት ዓመት በጀት ጋር ሲነጻጸር ከ111 ቢሊዮን ብር በላይ ልዩነት አለው፤ 16 በመቶም ዕድገት ያሳየ ነው፡፡ ወቅቱን ያገናዘበና ያለፉትን ዓመታት የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን ታሳቢ ያደረገ ስለመሆኑ እንዲሁም በቀጣይ የሚመጣውን የኢኮኖሚ ሂደትም ከግምት ውስጥ ያስገባ በጀት እንደሚሆን ተገምቶ የተዘጋጀ መሆኑ ተገልጿል፡፡

**ምቹ ሁኔታዎችና የትኩረት አቅጣጫዎች**

የገንዘብ ሚኒስትሩ አጠቃላይ አገሪቱ ከኢኮኖሚና ከፊስካል አፈጻጸም አንጻር ያለችበትን ነባራዊ ሁኔታ በማስረዳት፣ 2015 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግሥት ዓመታዊ በጀት የተመሰረተባቸውን ታሳቢዎችና የበጀቱን የትኩረት አቅጣጫዎችንም ለምክር ቤቱ አብራርተዋል፡፡

የቀጣዮቹ ዓመታት የማክሮ ኢኮኖሚ ትንበያን እንደ መነሻ በመውሰድ በቀጣይ ዓመት ሰላም ሰፍኖ የማክሮ ኢኮኖሚው እይታም ከተግዳሮቶች የተላቀቀ በመሆን ለቀጣይ የኢኮኖሚ ዕድገትና ማክሮ ኢኮኖሚ ዕድገት ምቹ ሁኔታዎች እንደሚፈጠር ታሳቢ መደረጉን ሚኒስትሩ አስታውቀዋል፡፡

**የገቢ ምንጮች**

በዝርዝር የቀረበው የ2015 ዓ.ም አጠቃላይ ገቢ የውጭ እርዳታን ጨምሮ 477 ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር እንደሚሆን መታቀዱን ሚኒስትሩ አስታውቀዋል፡፡ ከዚህም ውስጥ ከአገር ውስጥ ምንጭ የሚሰበሰበው ገቢ 92 በመቶ የሚሆነውን ትልቁን ድርሻ እንደሚይዝ ገልጸዋል፤፤ ከታቀደው የአገር ውስጥ ገቢ ብር 400 ቢሊዮን ብር ወይም 84 በመቶ የሚሆነው ከታክስ ገቢ ለመሰብሰብ የታቀደ መሆኑም ተገልጿል፡፡

ታክስ ካልሆኑ የገቢ ምንጮች የሚሰበሰበው ገቢ ሌላኛው የፌዴራል መንግሥት የወጪ በጀቱን ለመሸፈን የታቀደ የገቢ አይነት ሲሆን፣ በዚህም መሰረት በ2015 ዓ.ም ታክስ ካልሆኑ ምንጮች 38 ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዷል፡፡ ከዚህ ምንጭ የሚሰበሰበው ገቢ በዋናነት ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክና ከሌሎች ተቋማት የሚገኝ ገቢ ነው፡፡ ይህም በ2014 በጀት ዓመት ከተያዘው የ10 በመቶ ጭማሪ እንደሚኖረው ተጠቁሟል፡፡

ከገቢ አንጻር ለ2015 በጀት ዓመት መሸፈኛ የሚውለው የገቢ ምንጭ ከውጭ እርዳታ ምንጭ እንደሚገኝ የታቀደ ገቢ ሲሆን፣ ከዚህ ምንጭ ጠቅላላ ብር 38 ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ብር ለማግኘት ታቅዷል፡፡ ከዚህም ውስጥ ብር ሰባት ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር በቀጥታ ወደ መንግስት ማዕከላዊ ቋት የሚፈስ ሲሆን፣ ቀሪው ብር 31 ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር ለተወሰኑ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ በእርዳታ የሚገኝ እንደሆነም ተጠቅሷል፡፡

**የመደበኛና የካፒታል በጀት**

በረቂቅ በጀቱ ላይ ከተመለከተው ጠቅላላ የወጪ በጀት ውስጥ ለመደበኛ ወጪ ብር 345 ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር ለካፒታል ብር 218 ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር እንዲሁም ለክልል መንግስታት ድጋፍ ብር 213 ቢሊዮን እና ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ብር 14 ቢሊዮን ተደግፎ ቀርቧል፡፡

አጠቃላይ ተደግፎ ከቀረበው የፌዴራል መደበኛና ካፒታል በጀት ውስጥ 37 ነጥብ አምስት በመቶ ለመንገድ፣ ለትምህርት፣ ለውሃና ኢነርጂ፣ ጤናና የከተማ ልማትና የግብርና ዘርፎች የተመደበ ነው፡፡ ለእነዚህ ዘርፎች በ2014 በጀት ዓመት ከተደለደለው በጀት ድርሻ አንጻር የበጀት ድርሻው ቅናሽ ያሳያል፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት ለዕዳ ክፍያ፣ ለመከላከያ፣ ለመልሶ ማቋቋም፣ ለዕለት እርዳታ እንዲሁም ለማዳበሪያና ለስንዴ ድጎማ የተመደበው የበጀት ድርሻ በመጨመሩ ሲሆን፣ ለእነዚህ የተመደበው በጀት መጠንም ብር 239 ቢሊዮን ወይም የጠቅላላ መደበኛ በጀቱ 69 በመቶ ነው፡፡

በአጠቃላይ ለመደበኛ ወጪ ከተደለደለው በጀት ውስጥ ብር 75 ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ወይም 218 በመቶ ለደመወዝ፣ ለአበልና ለልዩልዩ ክፍያዎች እንዲውል የታቀደ ሲሆን፣ ብር 271 ነጥብ አምስት ቢሊዮን ወይም 78 ነጥብ ሁለት ደግሞ ለሥራ ማስኬጃ የተደገፈ መሆኑ ተገልጿል፡፡

ለበጀት ዓመቱ ከተያዘው በጀት ውስጥ 213 ነጥብ 4 ቢሊዮን የተጣራ የበጀት ጉድለት እንደሚገጥመው የተተነበየው ይሄው ረቂቅ በጀት በአገር ውስጥ እና በውጭ በሚወሰድ ብድር እንዲሸፈንም ታቅዷል። በሁለት አሃዝ ባደገ የዋጋ ንረት የታመመው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከ 2011 እስከ 2013 ዓ.ም በነበሩት ሦስት ዓመታት ውስጥ ከእቅድ በታች የሆነ የሰባት ነጥብ አንድ በመቶ አማካይ ዕድገት ማሳየቱም ተገልጿል።



ፎቶ ፎቶ፡- ገበበ ገብሬ

የገንዘብ ሚኒስትር አህመድ ሽዴ

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ፍቅር ራስን ከመሆን የሚጀምር ነው

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ከገነት ስፍራዎች አንዱን የሚመስል፣ የመላዕክት ስውር ሹክሹክታና ጽሞና የሚደመጥበት ከሰባቱ ሰማያት አንዱን የወረሰ፣ በአይን እየገባ ከነፍስ የሚያርፍ በደስታ እቅል የሚያሳጣ ቦታ፣ ነጭ አረፋውን እየደፈቀ በጌጣም ድንጋዮች ላይ የሚቦርቅ ፏፏቴ፣ እንደ ገረገራ በረድፍ በበቀሉት ዛፎች ላይ የሚዘምሩ አእዋፋት..በዚህ ሁሉ ውስጥ ለብቻዋ የተቀመጠች አንዲት ሴት። አይኗን ወደ ወንዙ፣ ጆሮዋን ወደ አእዋፍቱ፣ ቀልቧን ወደ ነፋሱ ሰዳ ከራሷ ጋር የጸሞነች። ወንዶች ያዩዋታል..በዛ ስፍራ ከእሷ ሌላ አይን ማረፊያ የሌለ እስኪመስል ድረስ። በዛ ስፍራ እሷ እንደ ጨረቃ ናት..እንደ ጀምበር። ሁሉም ወንዶች እሷን መሬት አድርገው የሚኖሩ ናቸው። ይሄ ያስጠላታል..ከወንዶች ሽሽት ያልደረሰችበት የብቸኝነት ጥግ የለም። ከወንዶች ሽሽት ያልቀለሰችው የብቻ ጎጆ የላትም። ግን ሁሉም ጽሞናዋ፣ ሁሉም የብቸኝነት ጎጆዋ በወንዶች የሚፈርስ ነው።

አጠገቧና ከአጠገቧ ራቅ ያሉ ጎርናና ድምጾች ይሰሟታል። ሁሉም ድምጾች ሴት ለማጥመድ፣ ሴት ለማሰናከል የሚያንሾካሹኩ ናቸው። እነኚህ ድምጾች ዘመኗን ሙሉ ስትሸሻቸው፣ ዘመኗን ሙሉ ስትጸየፋቸው የኖረቻቸው ናቸው ግን ሽሽተዋት አያውቁም። ባለችበት ሁሉ አሉ። ሀሳቧን ሳትጨርስ ወደ እሷ የሚደነቃቀፍ የወንድ ኮቴ ሰማች። ወዲያው በጥብቆዋ ያልተሸፈነ ገላጣ ማጅራቷ ላይ አንድ እጅ አረፈባት። ወደ ኋላዋ ስትዞር የሰማይ ስባሪ ከሚያክል ጎረምሳ ጋር ተገናኘች። ወጠምሻው በአይኑም፣ በጥርሱም እየሳቀ እጅ ነሳት። አስከትሎም ‹እርግጠኛ ነሽ የዚህ ግቢ ጠባቂ መላዕክት ነሽ?

‹አይደለሁም። መለሰችለት።

‹እሺ ከዘጠና ዘጠኙ ነገደ መላዕክት አንዷን ትሆኚ?

አይደለሁም።

‹ኪሊዮፓትራን አሊያም ደግሞ የዳቪንቺ ሞናሊዛ ነሽ እወራረዳለሁ?

‹አይደለሁም።

‹ኦ አወኩት! ይሄን ምሽት አብሮሽ የሚያሳልፍ እንደ እኔ ያለ ወንዳወንድ እየጠበቅሽ ነው አይደል?

‹አይደለም።

‹ይሄን ሁሉ ካልሆንሽ ታዲያ ምንድነሽ? መቶ ሃያ ሚሊዮን ሕዝብ ባላት ሀገር ላይ ብቻሽን ምን እየሠራሽ ነው?

‹‹ብቻዬን አይደለሁም..አየህ ብቻዬን እንዳይደለሁ እንኳን ማወቅ አልቻልክም። ልብ ቢኖርህ ኖሮ ብቻዬን እንዳልሆንኩ ትደርስበት ነበር።

በንግግሯ የበለጠ እየሳቀ ‹ታዲያ ከማን ጋር ነሽ? ከአንቺና ከክፍት ወንበርሽ በቀር እኮ አብሮሽ ማንም የለም›።

‹ሰው ብቻውን ሆኖ አያውቅም። እንደ ራስ ሙሉነት የለም። ከራስ ጋር እንደመሆን፣ ከራስ ጋር እንደማውራት በሰዎች መከበብ የለም። እኔም አሁን በራሴና በሀሳቤ፣ በጽሞናዬም የተከበብኩ ሴት ነኝ። ስለምን ብቻሽን ነሽ ትለኛለህ?

‹መግደርደሩን ተይና ቅረቢኝና ሴትነትሽን ሙሉ አድርጊ። አላት ጉራና ማን አለብኝነት በቀላቀለ ድምጽ።

‹እስካሁን ሙሉ ነኝ ይልቅ ከቀረብኩህ ነው የምጎለው..

‹ምን እያልሽ ነው? የትኛዋም ሴት እኔን ቀርባ ጎላ አታውቅም። እኚህ ሁሉ ሴቶች እኔንና የአንቺን እንቢ ማለት ነው የሚጠብቁት› አላት በዙሪያቸው ወዳሉት ሴቶች እየጠቆመ።

‹እንግዲያውስ ወደነሱ መሄድ ትችላለህ..አንድ ነገር ግን አስታውስ..እኔ ከነሱ ሌላ ነኝ፣ እኔ ካየሀቸው ሁሉ ሌላ ነኝ። እኔ በሕይወትህ ተመኝተህ ያጣሀት ሴት ነኝ። እኔ ማንም ፈልጎ የማያገኛት ሴት ነኝ። እኔ የትኛውም ወንድ ካለፍላጎቴ ምንም የማያደርገኝ ሴት ነኝ። እኔ ለእንዳንተ አይነቱ ከነውር ውጪ ምንም ለሌለው የሚሆን ልብ የሌለኝ ሴት ነኝ። እኔ በወንድ ልጅ መልክና ቁመና፣ ሀብትና ዝና ክብሬን አሳልፌ የማልሰጥ ሴት ነኝ። እኔ በሕይወትህ ባወኳትና በቀረብኳት ሚስቴም በሆነች ብለህ የተመኘሀት ሴት ነኝ። እኔ ሀብትህን መንዝረህ፣ እድሜህን ቆጥረህ የማትደርስባት ሴት ነኝ። እኔ የወንዶች ሁሉ ህልም ነኝ..ዳግመኛ እንዲህ እንደአሁኑ ፊቴ እንድትቆም እንኳን እድል አልሰጥህም› አለችው።

ሲያደምጣት በእልህ ነበር። የትኛዋም ሴት እንዲህ ብላው፣ እንዲህ ተናግራው አታውቅም። ወንድ አይደል የሆነ ሀሳብ መጣበት..ሴቶችን እንዴት መቅጣት እንዳለበት ያውቃል። ከእሷ ከምትበልጥ ሴት ጋር ወዳጅነት ፈጥሮ ሊያስቀናት ፈለገ እንዳሰበውም ፊቷ ብዙ አልቆየም ሽጋ ፍለጋ ወዲያ ወዲህ ጀመረ። አፍታ አልቆየም ግማሽ ደርዘን ሴቶችን ተዋወቀ። ከተዋወቃቸው ብዙ ሴቶች ጋር ፊቷ ላይ ብዙ ነገር ሆነ። ግን እንዳሰበው አልቀናችም..አለመቅናቷ ይበልጥ አበገነው። እኔ ስትል የተናገረችውን አምኖ መቀበል አልቻለም።

እሷ ረስታዋለች..ወደ ጽሞናዋ ከተመለሰች ዘመን የላትም። ወንዶችን ደግሞ ያለማሰብ ለነፍሷ ያስተማረቻት የልጅነት ጥበቧ ነው። አይደለም ደግማ ልታስባቸው አንድ ጊዜ የሚበዛባቸው የአፍታ ፍጥረታት ናቸው ትላለች። የቀረባት ሁሉ ግን ሳያስባት፣ ሳይሰልሳት ቀርቶ አያውቅም። ወንዶችን የመዝለጫ ትልቁ የበቀል በትሯ ይሄ ነው...

ሁሉም ሴቶች ዓለም አላቸው። ወንዶች የገቡበት ዓለም አንድ ቆንጆ ሴት ወንድ በሌለበት አንድ አጠገቧ ማንም ‹እንደዛሬ ውብ ሰማይ አይቼ አላውቅም..አንቺስ አይተሽ ይሆን? አንድ ድምጽ ተሰማት። የጽሞናዋ ውቅያኖስ ተናወጠ። ቀና ስትል በከሰዓት በኋላዋ ጀምበር ጥላው የረዘመ አንድ ወጣት ጎኗ ቆሞ ነበር። ‹ጸሐይ የሌለ ፈጋለች፣ ጨረቃም ያለልማዷ በቀን ወጥታለች፣ ክዋክብትም በጨረቃ ዙሪያ እያረገዱ አሸወይና ይላሉ። ንፋስም አናስገባም ሰርገኛ ሲል ያዜማል ማንን ሊድሩ ይሆን? እርግጠኛ ነኝ የቀረብሽ ሙሽራሽ እኔ ነኝ። ወንበሮቹም እኔን እየጠበቁ አሁንም ክፍት ናቸው› ሲል አጠገቧ አረፍ አለ።

ምንም አላለችውም። የሆነ ስህተት እንደሠራች ደረሰችበት። ይሄን ወንድ ጎትተው ያመጡት እነዛ ባዶ ወንበሮች እንደሆኑ አልጠፋትም። ስለ ወንበሮቹ ሲያወራት ነበር አጠገቧ ሰው የሚፈልጉ ሁለት ባዶ ወንበሮች መኖራቸው ትውስ ያላት። ስህተት ሠርታለች። መቀመጥ የነበረባት አንድ ወንበር ላይ ወይም ደግሞ ሌሎችን ሰዎች በማይጋብዝ ስፍራ ላይ ነበር። አንዳንድ ጊዜ ችግሮቻችንን ራሳችን ነው የምንፈጥራቸው። እነዛ ባዶ ወንበሮች ማሰብ ለማይችሉት ወንዶች ሰው እፈልጋለሁ ብቻዬን ነኝ ከማለት ሌላ ትርጉም አልነበራቸውም። ላያቸው ሁሉ መልዕክታቸው ያ ነው። ሰው ጤናማና ደስተኛ መሆን ከፈለገ ዘሪያውን ማጽዳት አለበት። እሷ ዙሪያዋን ሳታጸዳ ነበር ከወንዶች ሽሽት የጀመረችው። ከዚህ በፊት ለወንዶች የሚያጋልጣትን ውበቷን፣ ሰውነቷን፣ አይንና ተክለ ቁመናዋን ስትወቅስ ነበረች። አሁን ደግሞ ሁለት ወጠምሻ ወንዶችን ይዘውባት የመጡትን እነዛን ባዶ ወንበሮች ተቀየመቻቸው። ቢሆንም ግን የራሷ ፈላጭ ቆራጭ ራሷ ናት። ውበቷም ሆነ ሌሎች ነገሮች በእሷ ውሳኔ በኩል ሕልውና የሚያገኙ ናቸው።

አጠገቧ የተቀመጠው ወጣት ሊያማልላት የባጥ የቋጡን መለፍለፍ ጀመረ። በአንድ ጊዜ ጠላችው። ራሱን ያልሆነ ሰው አትወድም። ሰው መቼ ነው የሚያምረው ላላት ራሱን የሆነ ቀን ስትል የምትመልሰው መልስ አላት። ለሴት ልጅ ክብር ያለውና እውነተኛ ማንነቱን ይዞ የሚቀርባትን ወንድ እስኪታገኝ ድረስ የራሷ ናት። ለምትወደው የሚሆን ብዙ ፍቅር፣ ብዙ ክብርና ብዙ እውነት ያላት ሴት ነበረች። ሴት የራሷ ስትሆንና ሌላ ሁለተኛ ሰው በነፍሷ ላይ ስትሾም ሌላ ሁለት ዓለም ናት ትላለች። ሴት በሥርዓት፣ ወንድ በማሰብ ሲኖር ፍቅር ማለት ያ ነው ትላለች። ሴት ከገንዘብ ስትልቅ፣ ወንድ ከነውር ሲሸሽ አብሮነት ማለት ያ ነው ትላለች። ሴት ክብሯን ስትጠብቅ፣ ወንድ በጎነት ሲማር ጋብቻ ማለት ያ ነው ትላለች። ሴት ከውበት ስትርቅ፣ ወንድ ራሱን ሲሆን ትዳር ማለት ያ ነው ትላለች። ጨዋዋ ሴት።

# ዓለም አቀፍ



## ሩሲያ እና ቱርክ ከዩክሬን የእህል ንግድን ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ማድረስ በሚቻልበት ሁኔታ ላይ መከሩ

አዲስ አበባ፡- የሩሲያ እና የቱርክ መከላከያ ሚኒስትሮች ከዩክሬን የእህል ንግድን ወደ ውጭ መላክ በሚቻልበት እና በሶሪያ ወቅታዊ ሁኔታ ላይ በስልክ መክረዋል፡፡

ከየካቲት ወር ጀምሮ በሩሲያ እና በዩክሬን መካከል የተፈጠረው ግጭት ከሀገራቱ በጥቁር ባሕር በኩል በመርከብ ተጭኖ ሲወጣ በነበረው የእህል ንግድ ላይ እንቅፋት ፈጥሯል።

በዚህ ምክንያትም በዓለም አቀፉ የምግብ ፍጆታ በተለይም በጥራጥሬ ግብይት ላይ ከፍተኛ ጫና ፈጥሯል።


ቱርክ ሀገራቱ የእህል ወጪ ንግድ፣ የምግብ ዘይት እና ሌሎች የግብርና ምርቶቻቸውን ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ እንዲያቀርቡ ስምምነት ላይ እንደሚደረስ ያላትን ተስፋ መግለጿን ሲ ጂ ቲ ኤን ዘግቧል፡፡

የቱርክ መከላከያ ሚኒስትር ሁሉሲ አካር፥ በቀጠናው የሰፈነውን መረጋጋት ለማደፍረስ በሰሜናዊ ሶሪያ በሚንቀሳቀሱ የኩርድ አማጽያን እና አሸባሪዎች ላይ አስፈላጊው እርምጃ እንደሚወሰድ ለሩሲያው አቻቸው ሰርጌይ ሾይጉ ነግረዋቸዋል፡፡

የመከላከያ ሚኒስትሮቹ የሥልክ ውይይት የተካሄደው የቱርኩ ፕሬዚዳንት ሬሲፕ ታይፕ ኤርዶኻን ከሁለት ሣምንታት በፊት በቀጠናው በሚንቀሳቀሱ የኩርድ አማጽያን ላይ ወታደራዊ እርምጃ እወስዳለሁ ማለታቸውን ተከትሎ ነው፡፡

ቱርክ ጥቁር ባሕርን ከሩሲያ እና ከዩክሬን ጋር እንደምትዋሰን ይታወቃል፡፡

በተባበሩት መንግስሥት ጥረት የሩሲያ እና የቱርክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች በአንካራ ተገናኝተው የእህል ወጪ ንግድ ከዩክሬን በመርከብ ተጭኖ መውጣት በሚችልበት እና በሶሪያ ጉዳይ ላይ መምከራቸው ይታወሳል፡፡




## ቻይና አዲስ የጨረቃን ካርታ አስተዋወቀች

አዲስ አበባ፡- ቻይና በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ጥራት አለው የተባለውን አዲስ የጨረቃን ካርታ አስተዋውቃለች፡፡

ቻይና ያስተዋወቀችው አጠቃላይ የጂኦሎጂካል የጨረቃ ካርታ 1 ለ 2 ሚሊዮን 500 ሺህ የካርታ ስኬል መጠን ያለው ሲሆን እስካሁን ከነበሩት የጨረቃ ካርታዎች የበለጠ ጥራት አለው ተብሏል፡፡

የቻይና ተመራማሪዎች ከቻይና የጨረቃ ፍለጋ ፕሮጀክት እና ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች የተገኙ መረጃዎች እና የምርምር ግኝቶች ላይ በመመርኮዝ አዲሱን ከፍተኛ ጥራት ያለው የጨረቃ ካርታ ይፋ ማድረጋቸው ተመላክቷል፡፡

ካርታው ስለ ጨረቃ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ እና ስለ ጨረቃ ዝግመተ ለውጥ መረጃ የሚሰጡ አወቃቀሮች የተገጠመለት ሲሆን ለጨረቃ ሳይንሳዊ ምርምር፣ ለስነ ፈለክ እንዲሁም በጨረቃ ላይ የማረፊያ ቦታ ለመምረጥ ትልቅ አስተዋፅኦ ይኖረዋል ነው የተባለው፡፡

በቻይና የሳይንስ አካዳሚ የጂኦ ኬሚስትሪ ኢንስቲቲዩት ከቻይና ጂኦ ሳይንስ ዩኒቨርሲቲ እና ሻንዶንግ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር የጨረቃ ፕሮጀክቱን በመምራት ሲያስፈፅም እንደነበር ተገልጿል፡፡

ካርታው ግንቦት 30 ሳይንስ ቡሌቲን በተባለው እና በቻይና የሳይንስ አካዳሚ እና ከቻይና ብሔራዊ የተፈጥሮ ሳይንስ ፋውንዴሽን በጋራ በሚደገፈው ሳይንሳዊ መጽሔት ላይ መታተሙ ተመላክቷል፡፡

ቀደም ሲል ዩ ኤስ ጅ ኤስ የተባለው የስነ ክዋክብት ማዕከል በፈረንጆቹ 2020 1 ለ 5 ሚሊዮን በሆነ የካርታ ስኬል መጠን የጨረቃ ካርታ አጠናቆ ይፋ ማድረጉን ሲ ጅ ቲ ኤን በዘገባው አስታውሷል፡፡

# ስፖርት





## ዋልያዎቹ የፈርኦኖቹን ዘውድ ደመሰሱ

**ቦጋለ አበበ**

በ2023 የኮትዲቯር አፍሪካ ዋንጫ ለመሳተፍ ሁለተኛ የምድብ ጨዋታቸውን በገለልተኛ ሜዳ ማላዊ ላይ ከግብጽ አቻቸው ጋር ያደረጉት ዋልያዎቹ ታሪክ የማይዘነጋው ታላቅ ድል አስመዝግበዋል። ባለፉት አስራ አንድ አጋጣሚዎች ፈርኦኖቹን ገጥመው ሽንፈት እንጂ ድልን ቀምሰው የማያውቁት ዋልያዎቹ ዛሬ የፈርኦኖቹን ዘውድ ደምስሰው ታሪክ የማይዘነጋው ታላቅ ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ አበርክተዋል።




ዋልያዎቹ በፍጹም የጨዋታ ብልጫ ፈርኦኖቹን ከዙፋናቸው ለማውረድ ሙሉውን የጨዋታ ጊዜ መጠበቅ አላስፈለጋቸውም። በመጀመሪያው አርባ አምስት በዳዋ ሆጤሳና በሽመልስ በቀለ አማካኝነት ባስቆጠሩት ግቦች ከጨዋታው የሚፈልጉትን ውጤት ይዘው መውጣት ችለዋል። በፍጹም የራስ መተማመንና የአሸናፊነት መንፈስ ጨዋታውን ተቆጣጥረው የጨረሱት የአሰልጣኝ ውበቱ አባተ ልጆች ፈርኦኖቹን መግቢያ መውጫ አሳጥተው የኢትዮጵያን ሕዝብ ምሽት ፍሰሃ ሞልተዋል። ዋልያዎቹ ለውድድር የማይቀርበውን የኢትዮጵያና የግብጽ እግር ኳስ ደረጃን ግምት ውስጥ የከተተ ታሪካዊ ድል አስመዝግበዋል።

ይህ እንደ ማንኛውም ጨዋታ ድል ብቻ አይደለም። ለሁለቱም አገራት ትርጉሙ ብዙ ነው። ኢትዮጵያና ግብጽ የአፍሪካ እግር ኳስ ጠንሳሾች ናቸው። ይህን ታሪክ ይጋሩት እንጂ ዛሬ ላይ የሁለቱ አገራት የእግር ኳስ ደረጃ ልዩነቱ ሰፊ ነው። የደረጃ ልዩነቱ የቱንም ያህል ቢሰፋ ግን በተለያዩ ምክንያቶች የተቀናቃኝነት ስሜታቸው ለአፍታም ደብዝዞ አያውቅም። ሁለቱ አገራት የአለም ብሎም የአፍሪካ ጥንታዊ ስልጣኔ መገለጫ ከመሆናቸው ባሻገር በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎች የገጠሙት ጦርነትና የአባይ ወንዝ ትስስር በእግር ኳሱ መንደር ሲገናኙ ፍልሚያቸውን ይበልጥ ያጦዘዋል። በተለይም ሁለቱ አገራት ከታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታና ውሀ ሙሌት ጋር በተያያዘ ከቅርብ አመታት ወዲህ የገቡበት ውዝግብ ባላንጣነታቸውን አደባባይ እንዲወጣ ባደረገበት በዚህ ወቅት ድሉ ለኢትዮጵያውያን ያለው ትርጉም ከእግር ኳስም የበለጠ ነው።


## ከገፅ 28 የዞረ

| ተራ ቁጥር | የሥራ መደቡ መጠሪያ | የሥራ ደረጃ | የመደብ መታወቂያ ቁጥር | የወር ደመወዝ | ብዛት | ተፈላጊ ችሎታ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 23 | ሚድዋይፈሪ ፕሮፌሽናል I | XI | 14/አአ-አለ-2184፣ 2185፣ 2188 | 6193.00 | 3 | ከታወቀ የትምህርት ተቋም በአዋላጅ ነርስ ሙያ በቢ.ኤስ.ሲ ዲግሪ የተመረቀና 0 ዓመት የሥራ ልምድ፣ |
| 24 | የግዢ ባለሙያ IV | XII | 14/አአ-አለ-2527፣ 2528 | 7071.00 | 2 | የመጀመሪያ ዲግሪ በፐርቸዚንግ ማኔጅመንት፣ በማኔጅመንት፣ በአካውንቲንግ ወይም ተዛማጅ ሙያ፣ እና በግዢ የሙያ መስክ 6 ዓመት የሥራ ልምድ፣ |
| 25 | የግዢ ባለሙያ III | XI | 14/አአ-አለ-130፣ 131፣ 2530 | 6193.00 | 3 | የመጀመሪያ ዲግሪ በፐርቸዚንግ ማኔጅመንት፣ በማኔጅመንት፣ በአካውንቲንግ ወይም ተዛማጅ ሙያ፣ እና በግዢ ወይም ተዛማጅ ሙያ 4 ዓመት የሥራ ልምድ፣ |
| 26 | ፐብሊክ ሄልዝ ፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት I | XIII | 14/አአ-አለ-2622 እስከ 2626 | 8017.00 | 5 | በፐብሊክ ሄልዝ የትምህርት ዘርፍ በሁለተኛ ዲግሪ የተመረቀና 0 ዓመት የስራ ልምድ፣ |
| 27 | ደረጃ 3 ፕሮስቴቲክ ኦርቶቲክ ቴክኒሽያን I | VIII | 14/አአ-አለ-1519፣ 1520፣ | 3934.00 | 2 | ከታወቀ የትምህርት ተቋም በፕሮስቴቲክ ኦርቶቲክ በዲፕሎማ የተመረቀና 0 ዓመት የሥራ ልምድ፣ |

**በስራ መደቡ የሚሰጡ ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞች፡-** በሥራ መግቢያ መውጫ ሰዓት የሰርቪስ አገልግሎት ይሰጣል፣

**በምዝገባ ወቅት መቅረብ የሚገባቸው ማስረጃዎች**

በተራ ቁጥር 11፣12፣13፣19፣20፣23፣26 እና 27 ለተጠቀሱት የስራ መደቦች የሙያ ምዝገባና ፈቃድ የምስክር ወረቀት ማቅረብ ያስፈልጋል፣

የትምህርት ማስረጃና የስራ ልምድ ዋናውና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ

**የምዝገባ ቀንና ሰዓት፡-** ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት አሥር ተከታታይ የሥራ ቀናት ጠዋት ከ2፡00 እስከ 6፡00፣ ከሰዓት በኋላ ከ7፡00 እስከ 11፡00 ሰዓት ድረስ፣ ዓርብ ቀን የማዕከሉ የሥራ መውጫ 10፡00 ሰዓት፣ ለሁሉም የስራ መደቦች የሚቀርቡ ተወዳዳሪዎችን ፆታ የማይለይ መሆኑን እንገልፃለን።

**አድራሻ፡- አየር ጤና ሣይደርስ የቀድሞ ዘነበወርቅ ሆስፒታል፣ ስልክ ቁጥር 0118963821**

# አለርት አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል